# እንዘምር

## ወዖለ ኣንዝሬን ?



ልኡልሰገድ ለማ

በልዑልሰገድ ለማ

2012 ዓ.ም

*ይህንን መፅሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት ወይም ማሳተም ይቻላል።*

*አስተያየት ያላችሁ፡-*

*ኢሜል፡-leullema2009@gmail.com*

ፌስቡክ፡- Leulseged Lema

ቴሌግራም:- http፡//t.me/LeulLemaPulpit ወይም @LeulLemaPulpit

Scan The QR Code To Join Telegram Channel!

# ማውጫ


መግቢያ ..... 3
ምዕራፍ አንድ መዝሙር ..... 4
መዝሙር ምን ማለት ነው? ..... 4
የዝማሬ እና የዘማሪ መመዘኛ ..... 6
መዝሙርን ዘፈን ያላደረገው ምንድነው? ..... 10
ማጠቃለያ ..... 11
ምዕራፍ ሁለት ዘፈን ..... 12
ዘፈን ምን ማለት ነው? ..... 12
የሚዘፍን የዘፋኙን መንፈስ ይካፈላል ..... 13
“ዘፍ-ሙር” ዘፈን ነው! ..... 15
ማጠቃለያ ..... 16
ምዕራፍ ሦስት እየመረጥን እንዝፈን? ..... 17
የድኅረ ዘመናዊነት ጠባሳ ..... 17
በዘፈን በጎ ነገርን ብንናገርስ? ..... 18
ብሔራዊ “መዝሙር” እንዘምር? ..... 19
እየመረጥን አንዘፍንም! ..... 20
የማንዘፍንበት ስምንት ምክንያቶች ..... 24
ሦስት ምርጫ የለም ..... 30
ማጠቃለያ ..... 32
ምዕራፍ አራት ቤተክርስቲያን ምን ታድርግ? ..... 33
አማኞችን ደቀመዝሙር በማድረግ ..... 33
ዘማሪዎች ከቃሉ እንዲዘምሩ በማድረግ ..... 33
ለሙዚቀኞች ተገቢውን ትኩረት መስጠት ..... 34
እቅበተ እምነት አገልግሎት ማጠናከር ..... 34
ማጠቃለያ ..... 36
ዋቢ መጽሐፍት ..... 37

# መግቢያ

**በ**መዝሙርና በዘፈን ጉዳይ ሁሉም የወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት ተቋማት ወጥ አቋም አላቸው። *"ዘፈን ኃጢአት ነው፤ አማኝ መዝፈን የለበትም"* የሚል አቋም አላቸው። ከአብያተክርስቲያናት በሌላ ገጽታ ዘርዘር ድርገን የአማኞችን አቋም ብንመለከት በዋናነት በሁለት ልንከፍለው እንችላለን። በፐርሰንት ለማስቀመጥ ቢቸግርም አብዛኛው የወንጌላዊያ አማኞች የመሪዎቻቸውን አቋም ይጋራሉ። በጣም ጥቂቶች ደግሞ *"እየመረጥን እንዝፈን"* ይላሉ።

**በ**መዝሙርና ዘፈን ጉዳይ በጥያቄዎች የተወዛገቡ አማኞች አሉ። በብዛት ከሚጠየቁ ጥያቄዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡- *"እየመረጥን እንዝፈን?፣ ቅዱስ ዘፈን አለ?፣ አንድን የሙዚቃ ስራ ዘፈን ወይም መዝሙር የምንለው በምን መስፈት ነው?፣ ቋሚ መስፈትስ አለ?፣ በዘፈን በጎ ነገር ብናገር ምን ችግር አለው?..."* የሚሉ ናቸው። የተጠቀሱ ጥያቄዎችንና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን በቀጥታም በተዘዋዋሪ ለመመለስ አራት ምዕራፎችን አደራጅችያለሁ።

**በ**ምዕራፍ አንድ ስለ መዝሙር አጠቃላይ የሆነ ትርጉም፣ ጭብጦችና መለኪያዎችን ይተነትናል። የተነሱ ሀሳቦችን ለማጠቃለልም ተሞክሯል። ምዕራፍ ሁለት ደግሞ ስለ ዘፈን አጠቃላይ የሆነ ትርጉም፣ የዘፈን መዘዞች፣ ዘፋኝነትና ዘማሪነት እንዳይቀላቀል ይወተውትና የተነሱ ሀሳቦችን ለማጠቃለልም ተሞክሯል። ምዕራፍ ሦስት ደግሞ እየመረጥን እንዝፈን? ብሎ በመጠየቅ ይጀምርና የድኅረዘመናዊነት አስተሳሰብ በቤተክርስቲያን ላይ ይሳረፈውን አሻራ አጠር አድርጎ ይተነትናል፣ *"ብሔራዊ መዝሙር እንዘምር?፣ በዘፈን በጎ ነገር ብናገር ምን ችግር አለው?"* ብለው ለሚጠይቁ ሰዎችን የተቻለውን ይመልሳል። እንዲሁም እየመረጥን የማንዘፍንበትን ምክንያቶች ይዘረዝርና የተነሱ ሀሳቦችን ለማጠቃለል ይሞክራል። የመጨረሻው ምዕራፍ አራት ሲሆን በመጨረሻ ላይ ከቤተክርስቲያን ምን እንደሚጠበቅ እና ምን ማድረግ እንዳለባት ተንትኖ ያነሳውን ሀሳብ ያጠቃልላል።

**መ**ልሶችን እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮችን ከማውቀውና ከተለያዩ መጽሐፍቶች ያደራጀሁትን ለመማር ከፈለጋችሁ በትዕግስት እንድታነቡት በጌታ ፍቅር እግብዛችኋለሁ።

ከልዑልሰገድ ለማ

መልካም ንባብ!

# ምዕራፍ አንድ መዝሙር

**መ**ዝሙር ከአምላክ ዘንድ ለአማኞች የተሰጠ ውድ አገልግሎት ነው። ይህን አገልግሎት ስንፈጽም ኃይልን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንቀበላለን። አማኞች በዘመሩና ባመለኩ ቁጥር ኃይላቸው ይታደሳል። ያዘኑ ይጽናናሉ፣ ተስፋ የቆረጡ ተስፋቸው ይለመልማል፣ የደከሙ ይበረታሉ በአጠቃላይ ብዙ በረከትና ሰላም በአምልኮና በመዝሙር ውስጥ ይገኛል። ስለዚህ ይህ የከበረው አገልግሎት ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን። ለመሆኑ *"መዝሙር ማለት ምን ማለት ነው?"* ብለን እንጀምር።

## መዝሙር ምን ማለት ነው?

**"መ**ዝሙር የሚለው ቃል በተለያየ መልኩ ከአምልኮተ እግዚአብሔር (ለአምላክ ከሚቀርብ ማኅሌት) ጋር የሚገኖዳኝ ሲሆን፣ ዘፈን የሚለው ደግሞ ከዚህ ውጭ ያለው ሁሉ ነው።" (*ዶክተር ተሰፋዬ ሮበሌ*)

**ቋ**ንቋ የሰዎች ስምምነት ውጤት ነው። ከስምምነት ውጭ መኪናን መኪና ለማለት፣ ወንበርን ወንበር ለማለት፣ አህያን አህያ ለማለት አንዳች ምክንያት የለም። አንድ ቃል በሚወክለው ሐሳብ ወይም በሚያመለክተው ነገር ስንስማው ተግባቦት ይፈጠራል። የቋንቋው ተጠቃሚዎች፣ የቋንቋው ተግባቢዎች የአንድን ቃል ትርጉም የመወሰን እንዲሁም አማራጭ ትርጓሜውን የመለጠጥም ሆነ የማሳነስ ሙሉ መብቱ የቋንቋው ተጠቃሚዎች ነው።

**የ**አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ዘፈን እና መዝሙር ለሚሉት ቃላት ያቀረቡላቸው ገለጻ፣ በብዙ መልኩ አንድ አይነት ነው። እንዲያውም በአንዳንድ አውደ ምንባቦች ውስጥ፣ ሁለቱንም ቃል ያለአንዳች የትርጉም ለውጥ እያቀያየረ በተወራራሽነት ይጠቀማል። ነገር ግን በዘፈንና በመዝሙር መካከል መሰረታዊ ልዩነት አለ። ስለ ልዩነታቸው ከማየታችን በፊት መዝሙር ምን እንደሆነ እንመልከት።

**ዘ**ማሪ ጌታያውቃል "የዝማሬ እና የዘማሪ ልኩ" በሚለው መጣጥፍ *"መዝሙር ማለት ምን ማለት ነው?"* ብሎ ከጠየቀ በኋላ መዝሙርን እንደሚከተለው ገልጸውታል። *"መዝሙር በልባቸው ደስታን ተሞልተው የምሥጋናን መዝሙር በግላቸው ወይም ለሌሎች ለሚዘምሩ ሳይሆን የአምላካችንን መንግሥት በዝማሬ አገልግሎት አስፋፋለሁ ይሄ የኔ ጥሪዬ ነው ለዚህም*

*ደግሞ ስጦታውን ሰጥቶኛል ብለው በሰዎች ፊት ቆመው ዝማሬ ለሚያቀርቡ የተሰጠ ትርጓሜ ነው"*[1] ይላሉ፡፡

**መ**ዝሙር የሚለው ቃል “ዘመረ” አመሰገነ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ምስጋና ማለት ነው፡፡ መዝሙር በቤተክርስቲያን የዝማሬ ሥርዓት መሠረት በዜማ የሚቀርብ ምስጋና ነው፡፡ ምስጋና የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ እግዚአብሔር ክብሩ በባሕሪው ብቻ እንዳይቀር ስሙን እንዲቀድሱ ክብሩን እንዲወርሱ መላእክትንና ሰውን አስተዋይና አዋቂ አድርጎ ፈጥሮአቸዋል፡፡ ከቅዱሳን መላዕክት ወገን የነበረው ሉሲፈር ያልተሰጠውን አምላክነት በመሻቱና ምስጋና እንዲቀርብለት በመፈለጉ ከክብሩ ተዋርዷል፡፡ መዝሙር በአጋጣሚ የተጀመረ ሳይሆን ከአምላክ የተሠጠ የአገልግሎት ፀጋ ነው፡፡

“**መ**ዝሙር ማለት በአጭር ቋንቋ አገልግሎት ነው፡፡ ዓላማ ያለው፣ ግብ ያለው አገልግሎት ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር(በውዳሴ)፣ ወደ ሰዎች(በማነጽና በመጋበዝ፣ ወደ ራስ ውስጥም(በአምልኮ በጸሎት) የሚያመለክት መልዕክትን አስተላላፊ አገልግሎት ነው፡፡ መዝሙር የስሜት ማሟሟቂያ ሳይሆን አገልግሎት ነው፡፡ አገልግሎቱም መጽሐፍ ቅዱስንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ መለኮትን የተንተራሰ የማነጽ አገልግሎት ነው፡፡ ያላመኑትን ወደ ክርስቶስ የሚጠራና የሚጋብዝ፣ ያመኑትን እንደ ስብከት፣ ትምህርት፣ ትንቢት፣ ተግሳጽ፣ ምክር አገልግሎት ሁሉ የሚያንጽ፣ ከጌታ ጋር ያለንን ግንኙነትን የሚያጠናክር አገልግሎት ነው፡፡ መሠረተ ቃሉ ነውና ከቃሉ ጋር መጋጨት የለበትም፡፡ ማዕከሉና ትኩረቱ ጊዜያዊው ሳይሆን ዘላለማዊው መሆን አለበት፡፡”[2]

*“ዘምሩ፥ ለአምላካችን ዘምሩ፤ ዘምሩ፥ ለንጉሣችን ዘምሩ። እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና፤ በማስተዋል ዘምሩ። (መዝ 47፡6-7)*

**መ**ዝሙር ለአምላካችን ለንጉሳችን የሚቀርብ አገልግሎት ነው፡፡ መዝሙር ክርስቲያን በግሉ ወይም ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የሚዘምረው እና አምላኩን የሚያመልክበት ሲሆን የሚቀኘውም በልብ ነው፡፡

**መ**ዝሙር መንፈሳዊ ሲሆን ለእግዚአብሔር ክብር የሚዘመር፣ ከተቀደሰ ማንነት ለቅዱሱ አምላክ የሚቀርብ መስዋዕት፣ ውዳሴ፣ ምስጋና፣ አምልኮና ክብር ሲሆን በተጓዳኝነት መንፈሳዊ

---

[1] Getayawukal &Biruktawit Ministry 2014

[2] ከዘላለም መንግሥቱ “እንዝፈን ወይስ እንዘምር” ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ ነው፡፡ ርዕሱ ተቀራራቢ እንጂ ተመሳሳይ አይደለም፡፡ “ተመሳሳይ ቢሆንም ችግር የለበትም” ብሎኛል፡፡ ለበለጠ እውቀትና መረጃ መጽሐፉን ገዝተው ያንብቡ!

የሆኑ መልዕክቶች በዝማሬ ውስጥ ይቀርባል። መዝሙር ከሰው ለሰው ያልሆነ፤ ከሰው ለእግዚአብሔር የሆነ መስዋዕት፣ ውዳሴ፣ ምስጋና፣ አምልኮና ክብር ነው።

**በ**መዝሙር ለሰው ስለ አምላክ ይነገርበታል። መዝሙር ለሰው ከአምላክ ቃል ይመከርበታል። በመዝሙር ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይመሰገንበትም። በመዝሙር የሰው ማንነት እና ጀብደኝነት አይታወጅበትም። መዝሙር የአምላክን ፍቅር መግለጫ፣ መዝሙር የአምላክን ምህረት ማወጃ፣ መዝሙር ያዘኑ ሰዎችን እንደቃሉ በሆኑ ቃላት ማጽናኛ፣ መዝሙር ተስፋ የቆረጡ ሰዎችን በቃሉ ማበርቻ፣ መዝሙር የውስጥ መንፈስን በቃሉ እምነት ማንቂያ፣ መዝሙር ለነፍስ ጉልበት ማቀበያ፣ መዝሙር ሰዎችን ከተሳሳተ መንገዳቸው ውስጥ ዘልቆ በሚገባ ዜማ ኮርኩሮ እና አባብሎ ወደ ትክክለኛው መንገድ የሚመራ መሣሪያ ነው። ስለ መዝሙር? ስንት መባል ይቻላል ማነው ይህንን ጽሑፍ ከሚያነብ መሐል በመዝሙር ልቡ ተነክቶ ወደ ጌታ ያልመጣ? ማነው አዝኖ እና ተክዞ ዝማሬን ሲሰማ ተጽናንቶ ያልበረታ? ማነው ውስጡ የታፈነውን ደስታ በመዝሙር በጥቂቱ ቢሆን መተንፈስ ያልቻለ? ኧረ ማነው? መልሱ ማንም ነው። መዝሙር ከዘፈን ይለያል። መዝሙር መንፈሳዊ ኃይል አለው።

## <u>የዝማሬ እና የዘማሪ መመዘኛ</u>

**ሐ**ና ተክሌ *"ፍትሕ"* አለች፣ ቴዲ አፍሮ *"ለካ ሰው አይድንም በአራቱ ገደል፤ ወንጌል ይዞ መጥቶ ፍቅርን ያለ ገደብ"* አለ፣ በረከት ተስፋዬ *"እጅ እንንሳ..."* አለ፣ ዘሪቱ ከበደ *"ኦ ምን አገባኝ....እሱ አይሳሳት ሁሉን በምክንያት"* አለች፣ ሶፊያ ሽባባው *"የሰላም ሰው ነኝ"* አለች፣ የዘጸአት ኳየር *"ያገባኛል ይመለከተኛል"* አሉ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በምን አግባብ ነው አንዱ የዝማሬ አንዱስ የዘፈን ስያሜ ያገኘው? ዘፈንን ዘፈን፤ መዝሙርን መዝሙር የሚያደርጋቸውን መመዘኛዎች አብረን እንመልከት።

### 1. <u>የዘማሪው ማንነት</u>

**የ**ዘማሪው ሕይወት አገልግሎት ሊሆን ይገባል(ካነሳሁት ርዕስ ጋር እንድሄድ ስለፈለኩ እንጂ የሁሉም ክርስቲያን ሕይወት አገልግሎት መሆን እንዳለበት እሙን ነው)። አዎ ህይወት አገልግሎት ሲሆንና አገልግሎት ሕይወት ሲሆን የተለያየና እጅግም የተራራቀ ትርጉም አለው። አገልግሎት ሕይወት ሲሆን የቀለብ መሥፈሪያና የመድረክ ላይ ስራ ወይም አርት ይሆናል በተቃራኒው ህይወት አገልግሎት ሲሆን ደግሞ የተጻፈ መልዕክት ይሆናል።

**መ**ዝሙር ከሰው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ነው እንጂ በዚህ ዘመን እንዳለው(ሁሉንም ዘማሪዎች አያጠቃልልም) የገቢ ማሰባሰቢያና የዝና ማትረፊያ አይደለም።

**በ**እግዚአብሔር ፊት ያለ ነውር ራስን ጠብቆ በቅድስና መኖር ትልቅና ወሳኝ አገልግሎት ነው። አገልግሎት ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ትልቅ ኃላፊነት የሚጠይቅ አደራ።

*“በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ” (ቆላ 4፡17)*

*“ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።” (ሮሜ 12፡1)*

**አ**ንድ ዘፋኝ *“ኢየሱስ ያድናል…”* ብሎ ቢያቀነቅን እውነት ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ነው ነገር ግን ከሕይወት ለውጥ(ከዳነ ማንነት) የወጣ ስላልሆነ ዘፈን ነው። ምክንያቱም አምልኮ መስዋዕት ነው፣ ሕያውም ነው። ዘፋኝ ያዜመው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥም ሁሉ ዘፈን ነው። ምክንያቱም መዝሙር መንፈሳዊ ነው። መዝሙር ከተቀደሰ ማንነት የሚመነጭ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥምና ዜማ ነው። መዝሙር ካልተቀሰ ማንነት ሊመነጭ አይችልም! ሌላኛው ዘፋኝ *“ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነው…”* ብሎ ቢያቀነቅን እውነት ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ነው ነገር ግን ካልዳነ ማንነት የወጣ ስለሆነ ዘፈን ነው። እኛ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ *“ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነው…”* እንደምንለው በልቡ ያላመነ ሐሰተኛ *“ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነው…”* ማለት ይችላል(1ኛ ቆሮ 12፡3፣ ሉቃ 4፡34-35)። ምንጬን ስለምናውቅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ገሰጸው[3] ዘፈኑን አንቀበልም። ለምን? በጌታ በኢየሱስ አምኖ የተቀደሰ[4] ማንነት የለውምና። *“በኢየሱስ አምናለሁ”* እንኳ ቢል እውነተኛ የሕይወት ለውጥ ምስክርነት ሊኖረው ይገባል። ክርስቲና ስር ነቀል የህይወት ለውጥ ነው። ክርስቲና ጌታን መከተል ነው። ክርስቲና ጌታ በቃሉ ያዘዘንን መፈፀም ነው። ጌታ በቃሉ የከለከለውን አለማድረግ ነው። ዘፋኝ ካለበት የወደቀ ዓለም መላቀቅ አለበት። የዘፈን ሸክም ሊያራግፍ እና የጽድቅና የቅድስና ሸክም ሊሸከም ይገባል[5]። እንዲሁም የመንፈስ ፍሬ ሊገለጥበት ይገባል።

**አ**ንድን መዝሙር ለማጽደቅ የዝማሬው ይዘት ብቻ ሳይሆን በማን ተዘመረ? የሚለውም በጋራ መታየት አለበት። ስለዚህ መዝሙርን መዝሙር ከሚያሰኙት ውስጥ አንዱ የዘማሪው ማንነት ነው።

---

[3]የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄሃለሁ፥ አንተ <u>የእግዚአብሔር ቅዱሱ አለ</u>። ኢየሱስም፦ ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው። ጋኔኑም በመካከላቸው ጥሎት ሳይጐዳው ከእርሱ ወጣ። (ሉቃ 4፡34-35)

[4] ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ <u>ተቀድሳችኋል</u>፥ ጸድቃችኋል። (1ኛ ቆሮ 6፡11)

[5] እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ <u>እኔም አሳርፋችኋለሁ</u>። <u>ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ</u> ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና። (ማቴ 11፡28-30)

## 2. <u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥምና ዜማ</u>

*“ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤” (1ኛ ጴጥ 4፡11)*

**የ**ዝማሬ እና የዘማሪ መመዘኛ መሆን ያለበት የመዝሙሩ ግጥም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ወይስ አይደለም የሚል ነው። ግጥሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በተለይም አዲስ ኪዳናዊ መልዕክት ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ፡-

- ✓ መሲሃዊ ትንቢቶች እንዳልተፈጸሙ መዘመር የለባቸው።
- ✓ ሰውን ምድራዊ ብቻ የሚያደርጉ መዘመር የለባቸው። በሌላ አገላለጽ ክርስቲያኖች የከበረ ተስፋ እንዳላቸው መዘመር አለባቸው።
- ✓ ትምክህትን በሰው ስራ ወይም በፍጥረት ወይም በገንዘብ….ላይ የሚያደርጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉምና መዘመር የለባቸው።

**መ**ዝሙር የሰውን ኃጢአተኛነት፣ ደካማነት፣ ጨለማነትና ውድቀት ነግሮና ወቅሶ ወደ ክርስቶስ የሚመልስ መልዕክት ያለው ነው። መፍትሄው ክርስቶስ እንደሆነ የሚናገር ነው። መፍትሄውን ካለተናገረ ምንም ፋይዳ የለውም። ስለዚህ መዝሙሮች በግጥሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊነትም ጭምር መመዘን አለባቸው።

## 3. <u>የምትታነጽበት፣ ሌሎችም የሚታነጹበት መሆን አለባቸው</u>

**መ**ታነጽ ከውስጥ የሚጀምር ነው። ነፍስን በሚያረሰርስ ዜማ የተሰራ፣ ሰውን ወደ አምላክ ሕልውና የሚያስጠጋ መሆን አለበት።

*“እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን <u>ለማነጽ</u> እንዲበዛላችሁ ፈልጉ።” (1ኛ ቆሮ 14፡12)*

**እ**ውነተኛ መዝሙሮችን ለመለየት ከፈለጋችሁ *“ያንጻኛል ወይ?”* ብላችሁ ራሳችሁን መጠየቅ ነው። መልሱ *“አዎ እታነጽበታለሁ”* ከሆነ መዝሙሩን በጌታ ለሆኑ ወዳጆች ስትዘምር *“ይታነጹበታል? አይሰናከሉበትም?”* መልሱ *“አዎ”* ከሆነ በአራተኛውን መመዘኛ መዝነው። የማያንጽ ከሆነ መዝሙር አይደለም። አታድምጠው!

## 4. <u>መጸለይን ወይም ማምለክን ወይም ማመስገንን የሚያስከትል መሆን አለበት</u>

*“.... እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፥ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል። (1ኛ ጢሞ 4፡8)*

**ዜ**ማውን ስትሰማው እንድትጸልይ፣ እንድታመልክ፣ እንድታመሰግን ካላበረታህ ወይም ንስሃ እንድትገባ ካላነሳሳህ ይህ ዘፈን እንጂ መዝሙር አይደለም።

## 5. <u>እርስ በርስ የምንዘምረው ሊሆን ይገባል</u>

***“በ****መዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ <u>እርስ በርሳችሁ</u> ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ።” (ኤፌ. 5፡19)*

**በ**ልባችን መቀኘትና መዘመር ያለብን ለጌታ ነው። ይህ የተሰጠን ትእዛዝ ነው። በዘፈንና በዓለማዊ ቅኔ አልተባለም። የምንቀኝለትና የምንዘምርለት ጌታ አለ። የምንዘምረው እርስ በርስ እንጂ ከዘፋኞች ጋር አይደለም! *“በዚህ ዘመን ዘፋኞች ወደ ክርስቶስ ሲመጡ ዘማሪዎች ደግሞ ወደ ዓለምተኛ የዘፈን ሙያ ሲሄዱ ተስተውሎአል። ይህ የሙያ ቅይይር ብቻ ተደርጎ ከተወሰደ ስሕተት ነው። ይህ የማንነት ልውውጥ እንጂ የሙያ ዝውውር አይደለም። አንድ ክርስቲያን ወደ ዘፈንና ዘፋኝነት ሲሄድ ሥርዓተ እሴቱን ንቆ ነው። ያ ሥርዓተ እሴት ደግሞ መሠረቱ ቃሉ ነው።”*[6]

**የ**ትኛውም መዝሙር ከአምስቱ መስፈርት አንዱን ካላሟላ መዝሙር ሊሆን አይችልም። ከላይ የተጠቀሱ አራቱን መመዘኛዎች ካለፈ አምስተኛውን ማሟላት አለበት። አምስተኛው የመዝሙር መመዘኛ የምንዘምረው እርስ በርስ እንጂ ከዘፋኞች ጋር አይደለም! ክርስቲያኖች በሕብረታቸው ወይም በቤተክርስቲያን አምልኮ ስፍራ አብረው እርስ በርስ መዘመር የማይችሉ ከሆነ መዝሙር አይደለም። በተጠቀሱ አምስት መመዘኛዎች የማያሟላ ማንኛውም ግጥም ወይም ዜማ ዘፈን ነው።

---

[6] ከዘላለም መንግሥቱ “ዘፈን እና መዝፈን፣ ዘፋኝ እና ዘፋኝነት” ከሚለው ፅዝራ ልዩ ቅጽ ግንቦት ፪ሺህ ፰ ዓመተ ምሕረት MAY 2016 የተወሰደ።

## መዝሙርን ዘፈን ያላደረገው ምንድነው?

እንደሚታወቀው ዘፈንና መዝሙር ተመሳሳይ ግብዓቶችን (የሰውም ሆነ የመሳሪያ) የሚጠቀሙ ቢሆንም የሚቀርቡበት ዓላማና የሚገለጹበት መንገድ ግን ሁለቱንም በተናጠል የተለያየ ጎራ ውስጥ ይከታቸዋል። እንዲሁም ዘፈንና መዝሙር የተለያዩ ዓላማና ትግበራዊ አካሄድን የሚከተሉ ብቻ ሳይሆን ምንጫቸውም የተለያየ ነው።

“መዝሙርና ዘፈን ይዘታቸውን ይለያቸዋል። መዝሙር ትኩረት እንዳለው፣ የሚመለከ ጌታ ላይ እንድናተኩር እንደሚያደርገን፣ መልዕክት እንዳለው፣ ውደ ደኅንነት እንደሚጋብዝ፣ ዘፈንም ትኩረት አለው። ያስመልካል ክርስቶስን ግን አይደለም። መልዕክት አለው፤ ወንጌል ግን አይደለም። የሚመለከው ወይ ሰው ወይ ውበትና ቁንጅና ወይም ሀገርና ነጻነት፣ ግዑዝ ፍጥረት፣ ወይም ሰይጣንንም ሌላም ሊሆን ይችላሉ።”[7]

መዝሙር እንደ ማንኛውም ዘፈን በግጥም በዜማ የሚሆን እንጉርጉሮ ቢሆንም እንዲሁም መዝሙርንም ዘፈንም የምንጫወትበት መሳሪያ ተመሳሳይ ቢሆንም መዝሙርን ዘፈን የማያደርገው ብዙ ወሳኝ መሰረታዊ ነገሮች አሉት።

**መዝሙርን ዘፈን ያላደረገው፡-**

1. ከተለወጠ እና ከተቀደሰ ሁለንተናዊ ማንነት ከሰው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ስለሆነ፤
2. መዝሙሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልዕክቱም አዲስ ኪዳናዊ ስለሆነ፤
3. በእግዚአብሔር ላይ ተደጋፊ መሆናችንን ስለምንናገር፤
4. መዝሙር ሰዎች ለፈጠራቸው ባለቤታቸው ለሆነውና አምልኮ ለሚገባው ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሰጡ የሚመራ ስለሆነ፤
5. ሕይወታችን፣ እረፍታችን፣ በረከታችን፣ ተስፋችን፣ ክብራችንና ትምክህታችን እግዚአብሔር መሆኑን የምንናገርበት ስለሆነ፤
6. እውነተኛ ሰላም የሚገኘው ለእግዚአብሔር አምላክነት ስንገዛና እግዚአብሔር የፈጠረንን ዓላማ ስንከተል ብቻ እንጂ በተለያየ ቁሳቁስና ልምምድ የማይመጣ መሆኑን የሚናሳይበት በመሆኑ ከዘፈን በጣም ይለያል።

[7] ከዘላለም መንግሥቱ “ቤት ያጣው ቤተኛ ሕሳዊ ግምገማ” ቁጥር ፴፭ - ሐምሌ ፪ሺህ ፰ ዓመተ ምሕረት JULY 2016 ቅጽ የተወሰደ ነው። መጣጥፍ ከ http://books.good-amharic-books.com/EzMag.035.pdf ማግኘት ይቻላል።

# ማጠቃለያ

1. መዝሙር መንፈሳዊ ነው።
2. መዝሙር ከሰው ለሰው ያልሆነ፤ ከሰው ለእግዚአብሔር የሆነ መስዋዕት፣ ውዳሴ፣ ምስጋና፣ አምልኮና ክብር ነው።
3. መዝሙር ከተቀደሰ ማንነት የሚመነጭ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥምና ዜማ ነው።
4. የመዝሙሮች መመዘኛዎች፡-
   - ✓ የዘማሪው ማንነት፤
   - ✓ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥምና ዜማ፤
   - ✓ የምትታነጽበት፣ ሌሎችም የሚታነጹበት፤
   - ✓ መጸለይን ወይም ማምለክን ወይም ማመስገንን የሚያስከትል መሆን አለበት፤
   - ✓ እርስ በርስ የምንዘምረው መሆን አለበት።

# ምዕራፍ ሁለት ዘፈን

በዚህ ምዕራፍ ዘፈን ምን ማለት እንደሆነ፣ የዘፈን መዘዞች፣ "ዘፍ-ሙር" እንዴት ዘፈን እንደሆነ እንመለከታለን።

## ዘፈን ምን ማለት ነው?

"ዮናስ ጎርፌ በቃለ ምልልሱ[8] የመጨረሻ ክፍል ሊያስተላልፍ የሚፈልገው መልእክት ካለ ለተጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ *'አንድ ወጣት መጥቶ፥ 'ፓስተር፥ ዘፈን ኃጢአት ነው ወይስ አይደለም?' ብሎ ሲጠይቅ፥ 'ኃጢአት አይደለም፤ ይኼ ማለት ግን ሄደህ እበድ ማለት አይደለም' ብሎ የሚመልስለት አስተማሪ ያስፈልገዋል። እውነቱን ነግሮት ማለት ነው..."* ብሎአል። ይህ የጠቅላላው ቃለ መጠይቅ ማሰሪያ ሆኖ የቀረበ መደምደሚያ ቃል ነው።

ይህ ንጽጽር ዘፈን በተጠቀሰባቸው የመጨረሻዎቹ ጥቅሶች አብረውት ከተጠቀሱት ነገሮች ጋር ይሄዳል? አንድ ወጣት መጥቶ፥ *"ፓስተር፥ ጣዖት ማምለክ ኃጢአት ነው?"* ብሎ ቢጠይቀው፥ *"ኃጢአት አይደለም፤ ይህ ማለት ግን ለሞሎክና ለአርጤምስ አትስገድ እንጂ ለዛፉና ለወንዙ ብትሰግድ ምንም አይደለም"* እንደማለት አይሆንም? ክንድ ሰጥቶ ስንዝር መከልከል ስንዝር መስጠት እኮ ነው። ለዘፈን እርከን መስጠት ከተፈለገ እርከን አውጪው ማን ነው?"[9]

ሙዚቃ፣ ዘፈን እና መዝሙር የተለያዩ ናቸው። መዝሙር ሙዚቃ አይደለም፤ ዘፈንም ሙዚቃ አይደለም። ሁለቱም በሙዚቃ ይዋባሉ፣ ይታጀባሉ። ሙዚቃን ለመዝሙር መጠቀም ይቻላል እንዲሁም ለዘፈን መጠቀም ይቻላል። ሙዚቃ አማካይና ገለልተኛ ነው። ለጥሩም ለመጥፎም ነገር መጠቀም እንችላለን። ለጽድቅም ለኃጢአትም መጠቀም እንችላለን። ለመዝሙርም ለዘፈንም መጠቀም እንችላለን።

"ዘፈን በሚዚቃ መሳሪያ ይታጀብም አይታጀብም፥ መንፈሳዊ ያልሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ፣ የወንጌል መልዕክት ከቶም የሌለበት፣ የሰውን ውድቀትና ኃጢአት የማይናገር፣ የእግዚአብሔርን ክብርና የማዳኑ መንገድ የሆነውን ክርስቶስን ፈጽሞ የማያሳይ፣ መንፈሳዊነት የሌለበት፣ ዓለማዊ መልዕክት ያዘለ ዜማ ነው።

---

[8] የቃለ መጠይቁን የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በመጀመር ማየት ይቻላል፤ https://www.youtube.com/watch?v=NBIgPKbWk7Q

[9] ከዘላለም መንግሥቱ "ዘፈን እና መዝፈን፣ ዘፋኝ እና ዘፋኝነት" ከሚለው ዕዝራ ልዩ ቅጽ ግንቦት ፪ሺ፰ ፰ ዓመተ ምሕረት MAY 2016 የተወሰደ።

**ዘ**ፈን ሙያ ነው። እንደ ሙያ ዘፈን አካልን ብቻ የሚነካ ሙያ አይደለም፤ ስሜትን፣ ሕሊናን፣ አዕምሮን፣ ነፍስንና መንፈስንም ይዳስሳል። በጠቅላላው የሚታየውን ቁሳዊ አካላችንን ማስጨፈር ወይም ማንበርከክ ብቻ ሳይሆን የማይታየውን ስሜታዊ፣ ነፍሳዊና መንፈሳዊ ማንነታችንንም የመማረክና የመምራት ችሎታ አለው።”[10]

**ዘ**ፈን ማለት ምግባረ ብልሹነት የተጠናወተው ግጥም ወይም ዜማ እንዲሁም በጎ ግጥምና ዜማም ሆኖ የማናዜመው ቅኔ ነው። የማንዘፍነው መልካም ስላልሆነ ሳይሆን ስለማይጠቅመን፣ ስለማያንጸን ነው።

- **የ**እግዚአብሔርን ታላቅነት፣ የክርስቶስን ማዕከልነት፣ የቅዱሳት መጽሐፍት ባለ ሥልጣንነት ያላማከለ ዜማ ወይም ግጥም ሁሉ ዘፈን ነው።

**ከ**እግዚአብሔር ውጭ ደስታን ለማግኘት በሙዚቃ የሚደረግ ፈንጠዝያዎች ወይም ደስታ የማግኛ ጥረቶች ሁሉ ውድቅ ናቸው። ሙዚቃ ከእግዚአብሔር ውጭ ለሆነ ደስታ እንዳይውል በእግዚአብሔር ቃል ተከልክሏል(ሮሜ 14፡17)። እንግዲያው ምን ቀረልን? ለአምላክ ዝማሬ ከማቅረብ በስተቀር አንዳችም ምርጫ የለንም።

## <u>የሚዘፍን የዘፋኙን መንፈስ ይካፈላል</u>

*“መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤” (ኤፌ 5፡18-19)*

**ሐ**ዋሪያ ጳውሎስ የኤፌሶን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ እንዳይሰክሩ ይመክራቸውና ሀሳቡን በአራት ነጥብ አልቋጨውም ቀጠለና በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት በዝማሬ፣ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ በመዘመር፤ ለጌታ በልብ በመቀኘትና በማዜም እንደሚጠቅም ይነግራቸዋል። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት በአማኞች ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ እንዲሰራ መፍቀድ ነው። ከዚህ ክፍል በዋናነት የምንማረው በመንፈስ ለመሞላት አንዱ መንገድ መዘመር፣ መቀኘትና ማዜም እንደሆነ ነው።

**እ**ግዚአብሔርን የሚያመልኩ(የሚዘምሩ)[11] ከእግዚአብሔር ኃይልን ይካፈላሉ። ታስረው የሚዘምሩ ከእስራታቸው ይፈታሉ። ያዘኑ ይጽናናሉ፣ ተስፋ የቆረጡ ተስፋቸው ይለመልማል፣ የደከሙ ይበረታሉ፣ ብዙ በረከትና ሰላም በአምልኮና በመዝሙር ውስጥ ይገኛሉ።

---

[10] ከዘላለም መንግሥቱ “ቤት ያጣው ቤተኛ ሕሳዊ ግምገማ” ቁጥር ፴፫ - ሐምሌ ፪ሺህ ፰ ዓመተ ምሕረት JULY 2016 ቅጽ የተወሰደ ነው።
[11] መዝሙር የአምልኮ አንዱ ክፍል ነው።

የሚያመልኩ(የሚዘምሩ) ከእግዚአብሔር ኃይልን እንደሚካፈሉ[12] ሁሉ የሚዘፍኑ ከሰይጣን ኃይልን እንደሚቀበሉ እሙን ነው።

**የ**ሚዘፍን በዘፋኙ የሚሰራውን መንፈስ ይካፈላል። *"እንዴት ይካፈላል?"* ካላችሁ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ዲያብሎስ ስለሚያመሳስል ነው። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር እያመሳሰለ/Copy ይሰራል። የሙሴ በትር ወደ እባብነት ሲለወጥ ሐሰተኛውም ያመሳስል እንደነበረ እግዚአብሔርም መዝሙርን ቅዱስ አምልኮ እንዳደረገው፣ ዲያብሎስም ዘፈንን ርኩስ አምልኮ አድርጎታል።

**አ**ንድ ጤናማ ዘማሪ ግጥሞቹን ለመጻፍም ሆነ ለመዘመር የሚመራው በእግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን አንድን ዘፋኝ የሚመራው ደግሞ የዘፈን መንፈስ (ሰይጣን) ነው። አንደኛው ሰውንና ፈጣሪውን የሚያቀራኝ ሲሆን ሌላኛው ሰው ከፈጣሪው ጋር ያለውን ጤናማ ግንኙነት የሚያበላሽ ብሎም የሚያፈርስ አምልኮተ ጣዖት መገለጫው የሆነ ድርጊት ነው።

"**አ**ቴና(የግሪክ ዋና ከተማ) ያሉ በሕንጻ ኪነ ጥበብ የተዋበች ብትሆንም ሐዋሪያው ጳውሎስ የሕንጻ ኪነ ጥበብ በማድነቅ አልጀመረም። ይልቁን ሐዋሪያው ጳውሎስ እየዞረ ሲጎበኝ እንደ ቱሪስት ሕንጻዎችን አይደለም የሚያየው። በውስጡ ያሉ ጣኦታት ተመልክቶ *"መንፈሱ ተበሳጨበት"* ይላል። *'ለምንድነው ሐዋሪያው አርት የማያደንቀው?'* ከተባለ በውስጡ የተቋጠረ ክፉ ነገር ስላለ ነው። ሙዚቃን ክፉ መንፈስ እንደማይጣበቀውም ምን ማረጋገጫ አለን? በጎ ኃይላትም ክፉ ኃይላትም በሙዚቃ ላይ አይጣበቁም ወይ? በደንብ ይጣበቃሉ እንጂ! በሰው የሚያድሩ ከሆነ በሙዚቃ የሚያድሩበት ምን ምክንያት አለ? ስለዚህ መጠንቀቅ በጣም አስፈላጊ ነው።"[13]

---

[12] *"እግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሆነ ጊዜ ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር፤ ሳኦልንም ደስ ያሰኘው ያሳርፈውም ነበር፥ ክፉ መንፈስም ከእርሱ ይርቅ ነበር።"* (1ኛ ሳሙ 16፡23) ላይ በሳኦል ላይ ያረፈው ክፉ መንፈስ ዳዊት በገናን ሲመታ ደስ ይሰኝና ክፉ መንፈስም ከሳኦል ሲርቅ ነበር። ይህ የሚያሳየው በአምልኮተ እግዚአብሔር ኃይልን መካፈል እንዳለ ነው። ዘፈንም የሚዘፍን ከዘፋኙ ጀርባ ካለው መንፈስ ጋር እንደሚነካካ ማወቅ አለበት።

[13] ጋሽ ንጉሴ ቡልቻ በዘጸአት አፖስቶሊክ ቤተክርስቲያን "በዘፈን ጉዳይ" በተደረገ ፋናል ውይይት ሲያደርጉ ከተናገሩት የተወሰደ።

# "ዘፍ-ሙ-ር" ዘፈን ነው!

## ወይ ዘምሩ! አልያም ዝፈኑ! ለምን ትቀላቅላላችሁ?

በአንድ ወቅት ሐመልማል አባተና ቴዎድሮስ ታደሰ አዲስ አልበም የለቀቁበት ወቅት ነበር። እንዲሁም እነዚህ ሁለቱ ግለሰቦች አልበማቸው ውስጥ ለ"ፈጣሪያቸው" ምስጋና የሚያቀርብ አንዳንድ ግጥም አካተው ነበር።

በዘፋኝነታቸው ዓለም የሚያውቃቸው ሁለት ግለሰቦች ለፈጣሪያቸው ምስጋና ማቅረባቸው በራሱ ችግር ይኖረዋል ብዬ አላምንም። ማንኛውም ግለሰብ በገባውና በተረዳው መንገድ ፈጣሪውን ሊያወድስና ሊያመሰግን ይችላል። ነገር ግን በምንም ሁኔታ ዘፋኝ ያወጣው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኔ ብቻውን መዝሙር ሊሆን አይችልም። ሙዝሙርን መዝሙር ከሚያደርጉ መመዘኛዎች ውስጥ አንዱ የዘማሪው ማንነት ነው። ዘማሪም ዘፋኝም ለመሆን መሞከር ማብቃት አለበት። የሰረቁ አንዳንድ ሰዎች ከሕሊና ጸጸታቸው ለማምለጥ አስራት እንደሚከፍሉ የዘመኑ አዝማሪዎች ለዘፈናቸው መቀደሻ ቅዱሱን ቃል ባትጠቀሙ እንመክራለን። ይዝፈኑ፤ ምርጫቸው ነው። ግን ምናለ ቃሉን ብትተውት?

### በአንድ ጊዜ ዘማሪም አዝማሪም መሆን አይቻልም!

አዝማሪ የሚለው ስያሜ የመጣውና አገልግሎት ላይ መዋል የጀመረው ቀድሞ በቅዳሴና በዝማሬ አምላካቸውን ሲያወድሱ ቆይተው ጸጋቸውን በጣሉ፣ ክህነታቸውን አፍርሰው በየመኳንቱና መሳፍንቱ ቤት መዝፈን በጀመሩ ሰዎች ምክንያት እንደሆነ የሚገልጽ አንድ ቆየት ያለ ጽሑፍ ማንበቤን አስታውሳለው።[14]

### መች የወንጌሉን አደራና የቤት ሥራን ሰርተው ጨርሰው ነው ዘፈን ካልዘፈንን ሞተን እንገኛለን ብለው የሚሞግቱን?

ዘፍ-ሙ-ር(ዘፈንና መዝሙር) ዘፈን ነው። መካከለኛ መንገድ የለም። አንድ ቅኔ ወይ በመዝሙር ወይም በዘፈን ይመደባል። ምዕራፍ አንድ ላይ የተጠቀሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶችን ያሟላ ዘፋኝ ያወጣው ቅኔ ዘፈን ነው። ዘፍ-ሙ-ር መዝሙር አይደለም፤ መዝሙር ሊሆንም አይችልም። ዘፍ-ሙ-ር ዘፈን ነው።

[14] ሽመልስ ይ.(የነገረ ክርስቲያን መጽሔት ዋና አዘጋጅ)

# ማጠቃለያ

1. ዘፈን ማለት ምግባረ ብልሹነት የተጠናወተው ግጥም ወይም ዜማ እንዲሁም መልካምም ሆኖ የማናዜመው ቅኔ ነው።
2. ይዘትን በተመለከተ ዓለማዊ መዝሙር እንደሌለ መንፈሳዊ ዘፈንም የለም።
3. የሚዘፍን የዘፋኙን መንፈስ ይካፈላል።
4. ዘፍ-ሙር(ዘፈንና መዝሙር) ዘፈን ነው።
5. በአንድ ጊዜ ዘማሪም አዝማሪም መሆን አይቻልም።

# ምዕራፍ ሦስት እየመረጥን እንዝፈን?

በመዝሙርና በዘፈን ጉዳይ ሁሉም የወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት ተቋማት ወጥ አቋም አላቸው። *"ዘፈን ኃጢአት ነው፤ አማኝ መዝፈን የለበትም"*የሚል አቋም። ከአብያተክርስቲያናት በሌላ ገጽታ ዘርዘር ድርገን የአማኞችን አቋም ብንመለከት በዋናነት በሁለት ልንከፍለው እንችላለን። በፔርሰንት ለማስቀመጥ ቢቸገርም አብዛኛው የወንጌላዊያ አማኞች የመሪዎቻቸውን አቋም ይጋራሉ። በጣም ጥቂቶች ደግሞ *"እየመረጥን እንዝፈን"* ይላሉ እውነት እየመረጡ መዝፈን ይቻላል? በዚህ ምዕራፍ እንመለከታለን።

## <u>የድኅረ ዘመናዊነት ጠባሳ</u>

**"ድ**ኅረ ዘመናዊነት(Post Modern) በአጭሩ በአውሮፓ የተጀመረና አሁን በአሜሪካና በጠቅላላው ምዕራባዊ በሚባለው ዓለም ኃያልና ጨምዳጅ የሆነ ባህል ነው። ተጋቦቱ መላውን ዓለም ሰንጎ የያዘ ነው። ዋናው ትምህርቱ አዕምሮአችን የስሜቶቻችን ተርጓሚ ስለሆነ እኛ "እውነት" የምንለው ነገር ወይም ስሜቶቻችን "እውነት ነው" ያሉን ነገር ግላዊ። አንጻራዊና ሕላናዊ(Subjective) ብቻ ነው። "ፍጹም እውነት" የሚባል፣ ለሁሉም ሰውና በሁሉም ጊዜ እውነት የሆነ ነገር የለም የሚል ነው። ስለዚህም፣ በምንም ጉዳይ ላይ፥ ወሲብ ይሁን ጾታዊ ምርጫ፣ ጋብቻ ይሁን ፊቺ፣ ውርጃ ይሁን የክብር ሞት ወይም በእርዳታ መግደል(Euthanasia)፣ ብዙ ማግባት ይሁን ዘር ማጽዳት፣ ወዘተ ምንም ዓይነት ነባራዊና ግብረገባዊ እውነት ወይም መለኪያ ሊኖር አይችልም፤ አይገባም የሚል ባህል ነው። በድኅረ ዘመናዊ ባህል እሳቤ መሰረት ለኔ ትክክል የሆነው ነገር ትክክል ነው። ላንተም ትክክል የመሰለህ ትክክል ነው። ነውር ነገር የለም፤ ማንም ማንንም ማውገዝ የለበትም። ማውገዝ ራሱ የተወገዘ ነው።"[15]

**ክ**ርስቲና መስፈርት አልባ አይደለም። ድኅረ ዘመናዊነት *"እውነት አንጻራዊ ነው"* ብሎ የእውነትን ህልውና ይክዳል። ድኅረ ዘመናዊነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያን የሚሰብር፣ የእውነትን ካስማ የሚነቅል ከንቱ ፍልስፍና እና ኃይማኖት ነው። ይህ ፍልስፍና በቤተክርስቲያን ላይ እያሳደረ ያለው ከፉ ጫና በቅድስና እና ርኩሰት መካከል ያለውን ድንበር ደብዛ ማሳጣት ነው። *"በእኔ መረዳት"፣ "በእኔ አመለካከት ኢየሱስ ዘፈን ይወዳል"፣ "በእኔ መገለጥ"፣ "ሁሉም ባለው መረዳት ይመላለስ"፣ "እግዚአብሔር እኮ ፍቅር ነው"፣ "ምን አልባት"*....ወዘተ በሚል

---

[15] ከዘላለም መንግሥቱ እንዝፈን ወይስ እንዘምር" ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ።

አጉል አባባሎች ክርስቲያኖች መስፈርት አልባ እንድንሆን እያደረገ ነው። ብዙ አማኞች በቃልም በተግባር ፈር የለቀቁበት ጊዜ ላይ ነው።

## <u>በዘፈን በጎ ነገርን ብንናገርስ?</u>

**በ**ጎ የሚናገሩ ዘፈኖች እንዳሉ እሙን ነው። *"ክርስቲያኖች በጎ ነገር ቢዘፍኑ ምን ችግር አለው?"* ብለው የሚጠይቁ ሰዎች አሉ። ለዚህ ጥያቄ ጋሽ ንጉሴ ቡልቻ የሚከተለውን ይመልሳሉ።[16] *'በጎ ነገር ብንናገር መጥፎ አይደለም። በጎ ነገር ለመናገር መዝፈን አለብን ወይ? ነው የኔ ጥያቄ። በሌላ መንገድ መናገር አይቻልም ወይ?'* ብለው ጥያቄያዊ መልስ ሰጥተዋል። ቀጥለውም በጎ ነገር ከሚናገሩ ዘፈኖች *"ራስ ተፈሪያን"*ን እንደ ምሳሌ አንስተዋል። *"የራስ ተፈሪያንን አንዳንድ ሙዚቃዎች ስለ ማሕበራዊ ግንኙነት የሚናገሩ፣ ስለ ፍቅር የሚናገሩ ነገሮች አሉ። እነሱ ነገሮች መጥፎ ናቸው አልልም። የሚናገሩትን ነገር 'የሚናገሩበትን አውድ፣ የሚናገሩ ሰዎች ማንነት፣ ሰፈሩ ምድንነው?' ብየ እመረምራለሁ። ስለዚህ አንድ "ራስ ተፈሪያ"ን ስለ ወንድማማችነት ቢናገር 'አንተ ምንድነህ?' ብየ እጠይቀዋለሁ። ባዕድ አምልኮ ውስጥ የገባ ሰው ነው። አብዛኞቹ ሰው የሚያመልኩ ናቸው። የዕጽ ሱሰኝነትን የሚያበረታቱ ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ሰፈር ውስጥ ገብቼ በጎ ምክር ለመቀበል አልሄድም።"* ብለው *"በጎ ዘፈን እንዝፈን"* ለሚሉ "ደቂቀ ዮናስ"[17] ጥሩ ምክር ሰጥተዋል።

**ከ**ዚህ ርዕስ ጋር በተገናኘ በመጨረሻም ያነሱት ጋሽ ንጉሴ ቡልቻ *"አንዳንድ ቀን በዋልድባም ይዘፈናል' ይላሉ እነሱ። ምን ማለት ነው? ብዙ ቀን አይዘፈንም ማለት ነው። ዋልድባ ገዳሙ ለዘፈን የተመቸ አይደለም። ለጥሞና የተመቸ ነው፤ ግን <u>ያበድን</u>(አጽንኦት የግል) ቀን አንዳንዴ እንዘፍናለን ምንም አይደለም ማለት ነው። የእኛ ትውፊት በጣም ግልጽ ልዩነት አስቀምጧልል። መርጦ መዝፈን አይቻልም!"* ብለዋል።

**በ**አጭሩ ክርስቲያን በጎ ነገር መዝፈን የለበትም። መርጦ መዝፈን አይቻልም።

---

[16] ጋሽ ንጉሴ ቡልቻ በዘጸአት አፖስቶሊክ ሪፎርሜሽን ቤተክርስቲያን "በዘፈን ጉዳይ" ፋናል ውይይት ካደረጉት ውይይት የተወሰደ።
[17] "ደቂቀ ዮናስ" ማለት ዮናስ ጎርፌ እና ተከታዮቻቸው ማለት ነው።

## ብሔራዊ "መዝሙር" እንዘምር?

**ብ**ሔራዊ "መዝሙር" በተለምዶ መዝሙር እንለዋለን እንጂ ብሔራዊ ቃል ኪዳን ነው። የመዝሙር መስፈርትም አያሟላም። "የሕዝብ ወይም የባንዲራ መዝሙር በእንግሊዝኛ Anthem ይባላል። ጥንታዊው በእንግሊዝኛው ቃል የመጣው ከላቲን ሆኖ Antefn, Antifne, Antiphon, Antiphona ከሚባል ስርወ ቃል የወጣ ነው። Antiphone ዜማን ማስተዛዘል ወይም መቀባበል ሆኖ እንደ ጥያቄና መልስ የመሰለ በቃል ወይም በዜማ መቀባበልም ነው። ሕዝባዊ ወይም የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች እንደ ቃለ መሐላ ናቸው። ሁሌም የሚደጋግሙ ሲመረጡ ከሌሎች መዝሙራት ጋር ተያይተውና ተወዳድረው ወይም የአገሪቱ መሪ አካል ዜማና ድርሰቶች ታሪክ ከጥቂት መቶ ዓመታት በላይ አይርቁም። በሰፊው ሲታዩ የሀገርን በአንዳንድ ሀገሮች መዝሙሮች ውስጥ እግዚአብሔርም ስለ ጠባቂነቱ ይመሰገናል ወይም እንዲጠብቅም ይጸለያል።

**ብ**ሔራዊ 'መዝሙሮች' ቃል ኪዳኖች ናቸውና እጅ በትክክል ልክ አንሥቶ ወይም እጅ ደረት ላይ አድርጎ በቃል ይገራሉ። በአንዳንድ ሀገሮችም ቃል መግባት ወይም Pleadge ይባላሉ። በሌሎች ደግሞ በሙዚቃ ብቻ ይዜማሉ፤ ወይም በመሳሪያ ብቻ ታጅበው በቃል ይነበባሉ፤ ወይም በቃልና በሙዚቃ መሳሪያ ጭምር ሕዝቡ ቆሞ በዜማ ይዜማሉ። መቆም፣ እጅ ማንሳት፣ እጅ ደረት ላይ ማድረግ፣ ሌሎች የሚደረጉ ነገሮችን ሁሉ ማቆምና በተለይ ባለ ደንብ ለባሾች በተጠንቀቅ መቆም ብሔራዊ "መዝሙር"ን የተለየ ያደርጉታል።

**መ**ዝሙሩ ወይም ቃለ መሐላው ኖረም አልኖረም ክርስቲያን እንደመሆኑ መጠን ንጹህና ታማኝ ዜጋ እንዲሆን ቅዱስ ቃሉ ያስተምራል። ይህ ታማኝና ጤነኛ ዜግነት ግዴታን፣ መብትን፣ ኃላፊነትን፣ ሥልጣንንም በአግባቡ መተግበርን ይጠይቃል። ይህ ከክርስቲያን ይጠበቃል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህንን ቃል መግባት ወይም ቃልን ማደስ ወይም ብሔራዊ መዝሙርን መዘመር ከህደትና ኃጢአት ይመስላቸዋልና አይሉትም፤ አይዘምሩትም። ይህ የሕሊና ጉዳይ ስለሆነ የሰለጠኑትም ሀገሮች እነዚህን ኃይማኖተኞች ሰዎች መዝሙሮቹን ወይም ቃል ኪዳኖቹን እንዲሉና እንዲዘምሩ አይስገድዱም። አምባገነን በሆኑት ዘንድ ግን ግዴታ መሆኑ ይበልጥ ኃጢአት እንዲመስል ያደርገዋልና ኃይማኖተኞቹንም እልከኛ ያደርጋቸዋል። በአገራችን በደርግ ዘመን በዚሕ ጉዳይ የታሰሩ ክርስቲያኖች ነበሩ። አንዳንድ ክርስቲያኖች ክህደትና ኃጢአት ስለሚመስላቸው ብቻ ሳይሆን ዘፈንም ስለሚመስላቸው ላለማለት ይወስናሉ። ይህን የመረዳት ጉዳይ ስለሆነ በራሱ ክፋት የለበትምና እንደ ጤነኛ ዜጎች እስከኖሩ ድረስ ሊገደዱ የተገባ አይደለም። የሕሊና ነጻነት እምነትን መግለጥን ብቻ ሳይሆን አለመግባባትንም የሚያካትት

ነጻነት ሊሆን የተገባው ነው። ይህም ሆኖ፥ ይህችን አናሳ ሀሳብ ስደመድም፥ ብሔራዊ ወይም የባንድራ 'መዝሙሮች' በዘፈን ውስጥ የሚካተቱ ነገሮች አይካተቱበትምና ከዘፈን የማይምደብ መሆኑ የኔ መረዳት መሆኑን እሰምርበታለሁ።"[18] ብሔራዊ "መዝሙር" መዘመር ስሕተት ነው ብዬ አላስብም። በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን አቋም ብታወጣ ያወጣችውን አቋም ለመገዛት፣ አቋሜም ለማድረግ ሙሉ ፈቃደኛ ነኝ።

## <u>እየመረጥን አንዘፍንም!</u>

**ከ**ወራት በፊት *"ዘፈን ኃጢአት ነው? ኃጢአት አይደለም?"* የሚል የጦፈ ክርክር በአንድ ሕብረት ውስጥ ተካሄደ። ኃጢአት ነው ያሉትም ኃጢአት አይደለም ያሉትም ሽንጣቸውን ገትረው ሲከራከሩ ጥግ ላይ ሁኜ በሃዘኔታ እመለከታቸው ነበር። ምክንያቱም ዳር ሲነካ መሃል ዳር እንድሚሆን አስቀድሞ ገብቶኝ ነበራ ይላል የሮ መርጋ[19]።

**እ**ንዝፈን አንዝፈን የሚለው ክርክር ባለመስማማት ከተቋጨ ከሳምንት በኋላ *"ዘፈን ኃጢአት አይደለም"* ያሉት ተሰብስበው *"መርጠን እንዝፍናለን"* ብለው አወጁ ይላል ታሪኩን ያጋራኝ። *"ዘፈን ሙያ እንጂ ኃጢአት አይደለም"* ሲሉ ተደመጡ። ሳምንት ሳይቆይ ግን ለሚመረጠው ዘፈን መስፈርት ለማውጣት በድጋሚ ተቀመጡ። ከመጀመሪያው የባሰ ሰፊ ክርክር እንዳደረጉ ተሰማ። እንደውም አጀንዳውን ያቀረበው ልጅ የተመረጡት ዘፈኖች ያላቸውን የዘፈን ይዘቶች አቀረበ። *"ስለ ሃገር፣ ስለ ሰላም፣ ስለ ፍቅር...."* እያለ የተወሰነ ዘረዘረ። እርሱ እንደጨረሰ ግን ሁሉም እጁን ከማወራጨት በማይለያይ መልኩ አወጣ። ለአንደኛው እድል ተሰጠው፤ *"ስለፍቅር መዝፈን ከዝርዝር ውስጥ ለምን አልተካተተም? ማለት ስለተቃራኒ ጾታ ግንኙነት። ጋብቻ እኮ የእግዜር ሐሳብ ነው፤ የተቀደሰ ተቋም ነው፤ እናም በዚህ ዙሪያ የተዜመ ሙዚቃ ከዝርዝሩ መካተት ይኖርበታል?"* ብሎ ተቀመጠ። ሰብሳቢው ግን ይህ መዘፈን ከሌለባቸው ዝርዝሮች ውስጡ መሆኑን ተናገረ። ነገር ግን ከተወሰኑት ተቃውሞ ገጠመው። በመጨረሻ ዘፈንን የሚጥሉበትና የሚቀበሉበት ወጥ መስፈርት ማግኘት ባለመቻላቸው *"መርጦ መዝፈን"* የሚለውን ትተው *"መርጦ አለመዝፈን"* በሚለው ተስማምተው ተለያዩ። ሆኖም *"ዘፈን ኃጢአት ነው!"* ያሉት ወገኖች *"እንኳን ዘፈን መዝሙር እንመርጣን"* ብለው የሚናገሩት አሽሙር ነው የሚል ወሬ መናፈስ ጀመረ። የእንዝፍናለን ማህበርተኞች በምላሹ *"አንዳንድ ዘፈን ዘፈን ሳይሆን ዝማሬ ነው"* ብለው መሟገት ጀመሩ። በመጨረሻም ጉባኤቸውን ጠርተው እንዳይዘፈኑ

18 ከዘላለም መንግሥቱ "እንዝፈን ወይስ እንዘምር" ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ።

19 የሮ መርጋ የተባለ ታሪኩን ያጋራኝ ወንድሜ ነው።

ከተከለከሉት በስተቀር *"መልካም መልዕክት ያላቸው እንደመዝሙር መቆጠር አለባቸው"* ብለው ተስማሙ።

ይሄ ከሆነ ከወራት በኋላ ይኸው ዛሬ ማታ ወደ ቤቴ ስገባ ሶስቱን አገኘኋቸው።

**የሮ፡-** "ወዴት ነው በዚህ ማታ?"

"አልሰማህም የሙዚቃ ድግስ አለ?"

**የሮ፡-** "ኧረ? የሙዚቃ ድግስ ማለት?"

"ያው እየተቀወጠው ይታደራላ" አለ አንደኛው።

**የሮ፡-** "ዘፈን ልትዘፍኑ?" አልኳቸው

"መርጠን ነው የምንዘፍነው፤ እኛ ምንዘፍነው መልካም መልካሙን ብቻ ነው እርሱ ደግሞ መዝሙር በለው"

**የሮ፡-** "አሃ አዳር እየሄድን ነው በሉኛ"

"ማለት ይቻላል፤ ማይሆን ነገር አንዘፍንም፤ ለምሳሌ እግዚአብሔር የለም የሚል ዘፈን አንዘፍንም ሌላውን ግን እዘመራለን።"

ከእነርሱ ተለይቼ ወደ ቤቴ ሳቀና "ለአገልግሎት' እየሄዱ መሆናቸው ይሆን?" ብዬ ፈገግ አልኩኝ። ይላል የሮ መርጋ።

**ድ**ሮ ዘፈን ኃጢአት እንደሆነ ማንም ወንጌላዊ አማኝ ስለምያውቅ የመወያያ አጀንዳ አልነበረም። አጀንዳ መፍጠር ጀመሩ። *"ዘፈን ኃጢአት ነው ወይስ አይደለም?"* ክርክሩ በማሕበራዊ ሚዲያ ጀመረ። ቀጥለውም *"እየመረጥን እንዝፈን ወይስ በሙሉ እንተው?"* በሚሉት ክርክሩ ጦፈ። ብዙዎች *"ዘማሪ እግሌ ዘፍኖ የለ! ዘማሪት እገሊት ዘፍና የለች!"* እያሉ *"ዘፈን ኃጢአት አይደለም እየመረጥን እንዝፈን"* አሉ። ለምን ዘፈን ላይ ብቻ እንደሚያቆሙ አልገባኝም። አልኮል መጠጣትስ ተፈቅዷልን? መዘሞትስ ተፈቅዷል? ግብረሰዶምስ ኃጢአት ነው? እንወያይበት እንጂ ለምን በዘፈኑ ላይ ብቻ?

**በ**ዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን[20] እንደ አንድ የእምነት ተቋም ስህተቱን ስህተት ብላ ለመፈረጅና ለማውገዝ አቅም ያጣችበት ወቅት ነው ብዬ አሰባለሁ። በመሆኑም "ዘፈን" ዛሬ አደባባይ ላይ

[20] ቤተክርስቲያን የምለው "የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት" ለማለት ነው።

ወጥቶ እንደ ጽድቅ ድርጊት መቆጠርና በልበ ሙሉነት ለክርክር መነሻ ሀሳብ ሆኖ መቅረቡ፣ ቤተክርስቲያን ድርጊቱን ከጅማሬው ከእንጭጩ መቅጨት ያለመቻሏ ውጤት ነው ብዬ አምናለሁ። *"ግብረ ሰዶም ኃጢአት ነው አይደለም!"* ብሎ አደባባይ ወጥቶ የሚከራከር ወንጌል አማኝ ክርቲያን እንደሌለ *"ዘፈንም ኃጢአት አይደለም!"* ብሎ የሚከራከር ክርስቲያን እስኪጠፋ ድረስ ቤተክርቲያን መስራት አለባት ብየ አምናለሁ።

*"የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ <u>የኑሮአቸውንም ፍሬ</u> እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው።" (ዕብ 13፡7)*

**ሰ**ዎችን እንድንከተል አልተጠራንል። የተጠራነው የእምነታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንከተል ነው(ዕብ 3፡1)። እሱን እየተከተልን የእምነታቸውን ፍሬ እያየን አሁን በሕይወት ያሉ ሰዎችን ሳይሆን በሰዎች ውስጥ ክርስቶስን መከተል እንዳለብን ቃሉ ይናገራል። በኛ ውስጥ ክርስቶስን እንዲከተሉ(ያውን ያለንበት መንፈሳዊ እድገት ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ ብቻ) እንጂ የራሳችን ተከታዮች እንድናፈራ ቃሉ አይመክረንም። የራሳቸውን ተከታዮች(ደቀመዝሙርት) የሚያፈሩ ለመንጋው የማይራራ ጨካኞች ተኩላዎች ናቸው። መለያቸው ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስባሉ፣ የራሳቸውንም ታርጋ ይለጥፋሉ፣ ከኔ ከተለየህ ትሞታለህ ትጠፋለህ ይላሉ፣ ከክርስቶስ ይልቅ የራሳቸውን አባትነት ይስላሉ።[21]

**ክ**ርስቲያኖች እየመረጡ መዝፈን የለባቸውም፣ የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾችም እየመረጡ መሞዘቅ የለባቸውም። ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘፈን በሩ ዝግ ነው። ለዘፋኞች በሩ ክፍት ቢሆንም ዘፋኝነታቸውን አራግፎ ነው የጽድቅ ሸክም አሸክሞ ወደ ጉባዔው(ቤተክርስቲያን) የሚያስገባው። ቤተክርስቲያን ለዘፈንም ለዘፋኞች በሯን መዝጋት አለባት። ወንጌልን ሰብካ በሯን ሙሉ ለሙሉ መዝጋት አለባት። በወንጌል "እናንተ የኃጢአት ሸክም የከበደባችሁ ወደ እኔ ኑ" ብሏል ብላ ስለ ሸክም አራጋፊው ጌታ የምትሰብክ እንጂ ከኃጢአት ሸከመኛ ጋር አንድ ላይ አትሆንም። ስለዚህ ለዘፈን በሩ ሙሉ ለሙሉ መዘጋት አለበት። ለዘፈን "በተወሰነ ደረጃ ደርበብ ተደርጐ ይከፈት" ከተባለ ደርበብ ብሎ መከፈቱ፣ ሙሉ ለሙሉ ወለል ብሎ ከመከፈት ይልቅ፣ ዝርክርክ ነው።

**የ**አልኮል መጠጦችን እንጠጣ ወይስ አንጠጣ የሚለውም ክርክር፣ በይዘትም ሆነ በትንታኔው ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር በብዙ መልኩ ድንበርተኛም ነው። በስነ መለኮት፣ አንዱ አስተምህሮ

[21] ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ <u>ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ</u> ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ። (ሐዋ 20፡29-30)

ከሌላው ጋር እንደ ሰንሰለት የመያያዝ ጠባይ አለው። አንዱ ሲፈታ ሌላው ጸንቶ የሚቈምበት አቅም ወይም ባሕርይ የለውም። ምክንያቱም ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች በአንድም ሆነ በሌላ መልክ የመገናኘት፣ የመደጋገፍ፣ የመሰናሰን ባሕርዮት አላቸውና። ለዚህም ነው መናፍቃን በአንድ አስተምህሮ ሲስቱ፣ ያን አስተምህሮ በሳቱበት ቅጽበት፣ በበርካታ አስተምህሮዎች መንገድ ጥሰው የሚወጡት። በርግጥ መዝፈን ከጸደቀ፣ የዘፈን መንታ ወንድም የሆነው መጠጥና መጨፈር እንዲሁም መዘሞት እነሆ በደጅ ነው። ከዚያም ታናናሽ ወንድሞቹ ማጨስና መቃም፣ "ከልጅ ልጅ ቢለዩ ዓመትም አይቆዩ" በሚለው አካሄድ፣ የይገባኛል ጥያቄ የማቅረብ፣ ሙሉ መብት ይጐናጸፋሉ።

"**አ**ንዱን ፈቅዶ ሌላውን ወግድ ማለት በፍጹም አይቻልም። ሁሉን ደግፎ የያዘው መሠረት ከተናደ፣ በምን መሠረት ላይ ቆሞ እነዚህን ተጓዳኝ ጒዳዮች ወግድ ማለት እንደሚቻል አይገባኝም። በዚህ አንጻር ሲታይ ዛሬ እየተሟገትን ያለነው፣ በዘፈን ርእሰ ጒዳይ ላይ ብቻ አይደለም፤ ከእርሱ ጋር ተጓዳኝ በሆኑ ፈርጀ ብዙ ግብረገባዊ ርእሶች እንጂ[22]።

**እ**የመረጡ መዝፈን እጅግ ሲበዛ ውስብስብ ነው። መስፈርት ማዋቀሩ አስቸጋሪ የመሆኑን ያህል፣ ጒባኤ ጠረቶ፣ አገር ሰብስቦ፣ *"የትኛውን ዘፈን እንዝፈን? የትኛውን ደግሞ አንዝፈን?"* የሚለውን ጒዳይ መገምገም፣ ትልቅ አበሳ፣ ትልቅ አሳር ነው። ቤተ ክርስቲያን እንኳን ዘፈንን፣ መዝሙርን እንኳ በቅጡ ለመገምገም ጊዜ አግኝታ አታውቅም። ከዚህ ሁሉ ዝርክርክ አካሄድ ሁሉን ዘግቶ መቀመጡ የተሻለ ነው። በሩን ደርበብ አድርገን ከከፈትነው፣ *"ምን ያህል ይከፈት?" "ምን ያህልስ ይዘጋ?"* በሚለው ኅሊናዊ ፍርድ ከምንወዛገብ ሙሉ ለሙሉ መዝጋት፣ ዕዳው ገብስ ነው። ስለዚህ አማራጩ ደርበብ አርጎ መክፈት ሳይሆን፣ ሙሉ ለሙሉ መዝጋት ነው። ምክንያቱም በርካታ ኢሥነ ምግባራዊ የሆኑ፣ ከስነ መለኮታችን ጋር በቀጥታ የሚጻረሩ ትምህርቶች ስላሉ። ለዘመናት ዘግተን መቀመጣችን አንዳችም ነገር ካልጐዳን፣ ሕዝባችንም ይህን አሜን ብሎ ከተቀበለው፣ እንዲያውም ይህ የሙሉ ለሙሉ ማዕቀብ አካሄድ፣

---

[22] ተሟጋቾቻችን፣ "እኔ ስለዘፈን እንጂ ይህ ሁሉ ተያያዥ ጒዳይ አይመለከተኝም" ይሉ ይሆናል። ይህ ግን፣ "እኔ መንገዱን ልክፈት እንጂ፣ በመንገዱ ላይ በቋሚነት የሚመላለሱት እነማን ናቸው የሚለውን ሞራላዊ ጥያቄ ልጠየቅ አይገባም" እንደ ማለት ነው። ይህ ግን ስሕተት ነው። አንድ መድኀኒት አንድን በሽታ የመፈወስ ሙሉ ብቃት ኖሮት፣ ነገር ግን በጐን ጠንቁ አማካይነት ትቶት የሚሄደው በሽታ የሚበልጥ ከሆነ፣ እጩ መድኀኒት ሆኖ የቀረበው፣ በመድኀኒትነት ሊያገለግል የሚችል አይመስለኝም። ወገኖቼ፣ ዘፈን እንኳ ጥሩ ቢሆን (ጥሩ ነው የሚል አቋም ግን የለኝም)፣ ዘፈንን ተገን አድርገው፣ ዘፈን በቀደደው በር የሚገቡ የዘፈን አጫፋሪዎች፣ ትክክል ሊሆኑ አይችሉም (ወገኖቼ ዘፈንን የምናጸድቅበት አካሄድ ሌሎችን ለመኰነን አቅም ያሳጣናል እያልሁ ነው)። በዚህም አካሄድ ነው አብዛኞቹ የምዕራብ አገሮች ሁሉን አጽድቀው የተቀመጡት።

ኢኮኖሚያችንንና ጊዜያችንን ከታደገልን፣ ጠቃሚውን ነገር ከማይጠቅም ነገር ጋር ሳይሆን ጠቃሚውን ነገር ከሚጐዳ ነገር ጋር እያነጻጸርነው ነው ማለት ነው።[23]

## የማንዘፍንበት ስምንት ምክንያቶች

*"ክርስትያኖች ለምንድነው የማትዘፍኑት?"* የሚል ሰው ካለ ብያንስ ስምንት ምክንያቶች ስላለን አንዘፍንም።

### 1. ኃጢአት ስለሆነ

የሁላችን ምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማድረግ ያለብንን ሁሉ አስተምሮን አሳይቶን ነው የሄደው። ከኃጢአት በስተቀር በነገር ሁሉ ተፈትኗል። የእኛም የሕይወት መመሪያ እርሱን መምሰል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ሲዘፍን አላየንም። ሲዘምር ግን እናያለን። አትዝፈኑ ያለን የአምላክ ቃል ነው(ገላ 5፡21፣ 1ኛ ጴጥ 4፡3)። ይህን መረዳት ቤተክርስቲያን ያገኘችው ከቃሉ እንጂ ከኢትዮጵያ ባህል አይደለም።[24] ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊታችን ነው።

"ወንጌል ወደ አይሁድም ወደ አሕዛብ ሲገባ በመጀመሪያ የለወጠው ባህሉን አይደለም። ጌታ የሰጠው ታላቁን ተልዕኮ እንጂ ባህልን የመለወጥ ተልዕኮ አይደለም። በወንጌል የተለወጠ ማንነት ባህሉን ሊፈትሽና ከቃሉ ጋር ከተጣጣመ ሊቀበለውና አዲሱንና ዋናውን ተልዕኮውን ሊያሰርጽበት፤ ካልተጣጣመ ደግሞ ሊገፋውና ወዲያ ሊለው ይችላል፤ ይገባልም። ባህል በአዲሱ ማንነቱ ላይ በግዴታ ሊጫንበት የተገባው አይደለም። ክርስቲና እና ባህል ለምርጫ ቢቀርብ መራጩ ክርስቲያን መምረጥ የሚገባው እምነቱን ነው። እምነቱ በባህሉ ላይ ጫና ሊፈጥር ይገባዋል እንጂ ባህሉ እምነቱን ሊቀርጽለት መልቀቅ ወይም መፍቀድ የለበትም። ባህል መልካም ገጽታዎች እንዳሉት ግልጽ ነው፤ ክርስቲና ግን በመላው መልካም ስለሆነ በባህሉ ውስጥ የሚገኙት መልካም ነገሮች በክርስቲና ውስጥ ቀድሞውኑ ይገኛሉ።"[25]

በጌታችንና በመድኃኒታችንና በኢየሱስ ክርስቶስ "ዝፈኑ!" ተብለን ስላልታዘዝን አንዘፍንም። ጽድቁን እና ቅድስናውን እንድንከተል የተጠራን ክርስቲያኖች አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ *"ኢየሱስ ይዘፍን ነበረ?፣ መርጦስ ይዘፍን ነበረ"* በፍጹም አልመረጠም፣ አልዘፈነም። *"የኢየሱስ*

---

[23] ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ "እየመረጥን እንዝፈን! እየመረጥንም እንሞዝቅ!" ከሚለው ቅጽ የተወሰደ ነው።

[24] የኢትዮጵያ ባህል ዘፈንን የሚያበረታታ እንጂ የሚኮንን አይደለም።

[25] ከዘላለም መንግሥቱ "ዘፈን እና መዝፈን፣ ዘፋኝ እና ዘፋኝነት" ከሚለው ዕዝራ ልዩ ቅጽ ግንቦት ፪ሺ፱ ፰ ዓመተ ምሕረት MAY 2016 የተወሰደ።

*ክርስቶስ ተከታይ ነኝ፣ ደቀመዝሙር ነኝ"* የሚል ለመዝፈን እንዴት ይዳዳል? መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ክርስቶስ አልዘፈነም፣ ዝፈኑም አላለንም። ቃሉም(መጽሐፍ ቅዱስ) ዘፈን የሥጋ ስራ ነው፣ ኃጢአት ነው ይለናል። ኃጢአት ስለሆነ አንዘፍንም።

## 2. <u>የእምነት አባቶች ስላልዘፈኑ</u>

**የ**እምነት አባቶች በዕብራዊያን ምዕራፍ አስራ አንድ የተጠቀሱ፣ የአዲስ ኪዳን ሐዋሪያት ሲሆኑ ካስፈለገ ፍሬያቸውን እየመረመርን የተቀበልናቸው በቤተክርስቲያን ታሪክ የሚጠቀሱ አዕማድ ተሐድሶአዊያን እና ሪቫይቫሊስቶች ናቸው። እነኚህ አባቶች አልዘፈኑም፣ ዝፈኑ ብለው አልመከሩንም፣ አላዘዙንም።

**ኢ**የሱስ ኢየሩሳሌምን አይቶ አለቀሰላት ይላል እንጂ ሰዎችን ሰብስቦ ዘፈነላትም አይልም(ሉቃ 19፡41)። ሐዋርያው ጳውሎስ ሲታሰር፣ ሲፈታ፣ ስለወንጌል ሲሰደድ፣ ህዝበ ክርስቲያን ሲጨፈጨፍ፣ ስለወንጌል እርሱና ሐዋርያት ሲንገላቱ...... መከራው እንዲቆም ዘፈን አወጣ እንዴ? ለወንጌል ስርጭት ወይም ሰዎች ጌታን እንዲያውቁ ብሎ ዘፍኗል እንዴ? በፍጹም አልዘፈነም! የእምነት አባቶች ዘፈን አይበጅም እንዳሉት እኛም አይበጅም እናላለን። ይህን የምንለው የአባቶችን ትውፊት ይዘን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ስለማይደግፈውም ጭምር ነው። በአጭሩ የማንዘፍንበት ሁለተኛው ምክንያት የእምነት አባቶች ስላልዘፈኑ ነው።

## 3. <u>ከማንነታችን ጋር ስለማይሄድ</u>

*"ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?" (2ኛ ቆሮ 6፡14)*

**እ**ግዚአብሔር ስለፈጠረን እናመልከዋለን፣ አምልኳችን ማንነታችን ነው። እግዚአብሔርን ባመለክን እና በዘመርን ማንነታችን ምንዘፍንበት ምንም ምክንያት የለም። ዘፋኝነት ኃጢአት ነው። ኃጢአት ደግሞ ዓመጽ ነው። ጽድቅ ከዓመጽ ጋር ምንም ተካፋይነት የለውም።

## 4. ስለማያንጽ

**“ዮ**ናስ ጎርፌ "Critical Thinking" ቤተክርስቲያን ውስጥ መተግበር አለበት የሚለውን ስሁት አመለካካት የሚያራምድ ግለሰብ ነው[26]። ‘Critical Thinking’ የሚተገበረው ግን በአብዛኛው በሂሳብ ሳይንስ አመክንዮ(logic) እና በፍልስፍናው ዓለም ነው።

**ቤ**ተክርስቲያን የምትመረው ግን በ’Critical Thinking’ ሳይሆን በ’System Thinking’ ነው። ስለዚህም በ’Critical Thinking’ የሚመሩ ሰዎች በአብዛኛው የሙግታቸው ማጠንጠኛ ራሳቸው እንጂ ሲስተሙ አይደለም፣ ለምሣሌ ዮናስ ጎርፌ ዘፈን ይዘፈንለት እንጂ ቤተክርስቲያን እሱ በሚያራምደው ዕሳቤ ሺህ ቦታ ብትሸነሸን ግድ የማይሰጠው ሰው ነው...ልክ ንጉስ ሰለሞን ፊት የራሷ ያልሆነውን ልጅ ለሁለት ይከፈል እንዳለችው ሐሰተኛ እናት ማለቴ ነው። እውነተኛዋ ግን ‘System Thinker’ ነበረችና የራሷን ሙግት አቁማ ለልጇ ‘Organic wholeness’ ቅድሚያ ሰጠች...This is what we call system Thinking!

**ቤ**ተክርስቲያን ግን ‘Organic’ ነች። ሁላችን የክርስቶስ አካል እንጂ ነጠላ ማንነት የለንም። ስለዚህም የግላችንን ጉዳይ ይዞ ከመሮጥ በፊት ለዚህ ‘Organic system’ ማሰብን ቅድሚያ እንሰጣለን። ሐዋሪያ ጳውሎስ ሥጋን መብላት ወንድምህን የሚያሰናክል ከሆነ አትብለው ያለው ‘System Thinker’ ስለሆነ ነው። ሥጋን መብላት እኔን እየገነባ ሌላውን የአካል ክፍል የሚያቀጭጭ ከሆነ መተው ግድ ነው።”[27]

*“**ይ**ህ ሰው አንድ ቀን ከሌላ ቀን እንዲሻል ያስባል፥ ያ ግን ቀን ሁሉ አንድ እንደ ሆነ ያስባል፤ እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ። ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብራል....” (ሮሜ 14፡5-6)*

**ይ**ህንን ክፍል ቀናትን ለሚያከብሩና ቀኖች ሁሉ እኩል ናቸው ብለው የሚያምኑ ሰዎች ቦታ ላይ ዘፈን ለማስገባት የሞከሩትን ጋሽ ንጉሴ የሚከተለውን ብለዋል። *“ሮሜ 14 ላይ ያለውን አመለካከት ተክቼ ለማስገባት ሞከርኩኝ። ሰንበት እናክብር፣ አናክብር ብለው የሚጨቃጨቁ ሰዎችን ወንድማችን ጳውሎስ አንዱ ለጌታ ብሎ ሰንበትን ያከብራል፤ የጌታ ቀን ነው፣ የተለየ ነው ብሎ። አንዱ ደግሞ ጌታ ሁሉንም ቀን አንድ አድርጎ ሰርቷል ስል ለጌታ ብሎ አያከብርም። የሚበላው ለጌታ ስለ አመስግኖ ይበላል፤ የማይበላውም ስለ ጌታ ስል አይበላም የሚለውን*

[26] ዮናስ ጎርፌ “ቤት ያጣው ቤተኛ” የተሰኘ መጽሐፍ ጸሐፊ ሲሆን “እየመረጥን እንዝፈን፣ ዘፈን ኃጢአት አይደለም” የሚል ጠቅላላ አቋም አለው።
[27] ከኢንጂነር ጌታሁን ሔራሞ ፌስቡክ ገጽ የተወሰደ።

*ዘፈን የሚለውን ቃል ለማስገባት ሞክሬ "ዘፈንን ለጌታ ስል ይዘፍናል ለማለት በጣም ቸገረኝ! የዘፈን ምድብ/Category ከዛ ጋር በምንም አይገናኝም። ይልቁኑ ለአይሁድም፣ ከግሪክም፣ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ ይላል። ይህ ለክርስቲያኖች ማሰናከያ አልሆነም ወይ?"* ይህን ብለው ሀሳባቸው አላበቁም ይቀጥላሉ ጋሽ ንጉሴ *"ዘፈን እየዘፈንኩ እንዴት ያለ አምልኮ ለእግዚአብሔር አቀርባለሁ?"* ብለው ጉባዔውን ጠይቀው ነበር።

*"**የ**እግዚአብሔር ቤተመቅደስ እኛ አይደለንም ወይ? በደርግ ጊዜ የቤተክርስቲያኗ መዘምራን ልብስ እና የሙዚቃ መሳሪያ በመቀማቱ ምክንያት ለከነት ቡድን በመሰጠቱ በጣም እናለቅስ ነበረ። በጣም የሚያሳዝን ዘመን መጣ። ወሰዱብንኮ! ጊታራችንን ለከነት አዋሉ ኢያልን በጣም እናዝን ነበረ። ዛሬ የጊታርና የመሰንቆ ራሳችንን ለዘፈን እያዋልን እንደሆነ ነው የማየው። እንዴት የበለጠ ኢያሳሰብም? ነው የኔ ጥያቄ"* ብለው ቁጭታቸውን ከትዝታ ጋር ይነግሩናል። እውነትም ከደረጃችን ወርደናል።

**መ**ታነጽ ሁለንተናዊ ነው። ከውስጥ ማንነት ከመንፈስና ከነፍስ የሚጀምር ነው። ማነው ዘፈን ዘፍኖ እውነተኛ መታነጽ የታነጸ? ማነው ዘፍኖ ሌሎችን ያነጸው? "ቤት ያጣው ቤተኛ" የሚለው መጽሐፍ ከታተመና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከታደለ በኋላ በዘፈን አንድም ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲጠራና በማንኛውም ዘፈን ዓለም የተጨመረ አዲስ ነፍስ የለም። ይልቁን ሲሰናከሉ ነው የምናየው።

"**ከ**ቤተ ክርስቲያን ኮብልለው የጠፉ ዘፋኞች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እነዚህ ቢዘምሩ ማምለካቸው ነው ወይስ ገንዘብ መሥራታቸው? ከላይ እንዳየናቸው ከዓለም ተመንጥቀው ወደ ጌታ ጉያ የገቡም አሉ። እነዚህ ይህን ጌታ ቀምሰውት ተመልሰው ይዘፍናሉ? ወይስ ቀድሞውኑም አልቀመሱትም? እንደ ክርስቲያን የሕይወት ዓላማና ግብ አለን። ዓላማችን የእግዚአብሔር ክብር ነው። ግባችንም እንደየተሰማራንበት መስክ ሌሎችን ማነጽ ነው። ስለዚህ መጠየቅ ያለብን ጥያቄ፡-

1. ይህ ነገር እግዚአብሔርን ያስከብራል? እና
2. ይህ ነገር ሰዎችን ያንጻል? ይገነባል? የሚል ነው። ይገነባል ስንልም ዋናው ሊገነባ የተገባው የሰው ማንነት ከውስጥ ጀምሮ ወደ ውጪ የሚሰፋው ማንነቱ ቅደም ተከተል እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።"[28]

[28] ከዘላለም መንግሥቱ "ዘፈን እና መዝፈን፣ ዘፋኝ እና ዘፋኝነት" ከሚለው ዕዝራ ልዩ ቅጽ ግንቦት ፪ሺህ ፰ ዓመተ ምሕረት MAY 2016 የተወሰደ።

## 5. ከጥሪያችን ጋር ስለማይሄድ

**የ**ተጠራነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት እንድንካፈል፣ ደቀመዝሙር እንድንሆን፣ የንጉስ ካህናት እንድንሆን እና መስቀሉን እንድንሸከም ነው። “እኛ የንጉስ ካህናት ነን፤ ካህናት አይዘፍኑም። ቢዘፍኑም አያምርባቸውም። ካህናት መስውዕት ይሰዋሉ፣ ያሳርጋሉ፣ ይማልዳሉ፤ እርሱን የጠራቸውን ፈጣሪ ያዳናቸውን አዳኝ ያወድሳሉ፤ እንጂ ካህናት አይዘፍኑም። እኛ ካህናት ነንና አንዘፍንም፤ የዘፈነ ወይም ያስዘፈነ አንድ ካህን አለ፤ አሮን ይባላል። ያስዘፈነበት ታሪክ ከጣዖት አምልኮ ጋር የተቆራኘ ነው።”[29]

**መ**ስኩ ይለያይ እንጂ ጥሪያችን ባለንበት መስክ ክርስቶስን መስበክ ነው። ወንጌል ማሰራጨት ነው። እየዘፈነ ለሰው ሰብኮ እንዴት መመለስ ይቻላል? አይቻልም። የማንዘፍንበት አምስተኛው ምክንያት ሰውን ወደ መንግሥቱ ለማምጣት ምንም ስለማይጠቅም እና ከጥሪያችን ጋር ስለማይሄድ አንዘፍንም።

## 6. ከአምልኮ ጋር ስለማይሄድ

*“እንግዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ። ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፤ (1ኛ ቆሮ 5፡7)*

**የ**ማንዘፍነው የሁለት ተቃራኒ ዓለማት ሰዎች ስላልሆንን ነው። ክርስቶስ እና ዲያብሎስ አንድ እንዳልሆኑ ዘፈንና መዝሙር አንድ ሊሆን አይችልም። *“የመቅደስ ከበሮ ለሰርግ አይዋስም”* እንዲል አገርኛው አባባል ሕያውን አገልግሎት በሙት መተካት ስለማንፈልግ ነው። ለማሕበራዊ ፍጆታ አልያም ለመቻቻል አልያም ለዓምልኮተ ጣኦት ሲባል ከወንጌል ዓላማ ውጪ በሆነ አካሄድ መሄድ በራሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ሁለቱን ቀላቅሎ ለማስታረቅ መሞከር እሳትና ጭድ በዘላቂነት እንዲኖሩ ለማድረግ እንደመሞከር ነው። አዲሱን ሊጥ ለመሆን አሮጌውን እርሾ ማስወገድ ግዴታ ነው። በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ ማኖር አይቻልም። በአሮጌው እርሾ አናምልከው። አምልኮን አንደባልቀው። ከቅዱስ አምልኮ ጋር ስለማይሄድ አንዘፍንም።

---

[29] ከዘላለም መንግሥቱ “ቤት ያጣው ቤተኛ ሕሳዊ ግምገማ” ቁጥር ፴፫ - ሐምሌ ፪ሺህ ፰ ዓመተ ምሕረት JULY 2016 ቅጽ የተወሰደ ነው።

# 7. ከወንጌል ምስክርነት ጋር ስለማይሄድ

*"የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና። በዚህም ነገር ወደዚያ መዳራት ብዛት ከእነርሱ ጋር ስለማትሮጡ እየተሳደቡ ይደነቃሉ።" (1ኛ ጴጥ 4፡3-4)*

"**ጴ**ጥሮስ የሚመክረን ያለፈው ዘመን ይበቃል። የተዳራችሁበት፣ የዘፈናችሁበት፣ እንዳሻችሁ የሮጣችሁበት ዘመን ይበቃል። አሁን ወደዚያ መዳራት ከነሱ ጋራ ስለማትሮጡ ከእናንተ ጋር ድሮ የሚሮጡ ሰዎች እየተሳደቡ ይደነቃል። ለምን? ልዩነቱ ታይቷቸው። ይደነቃሉ ደግሞም ይሳደባሉ። እኛ ልዩ በመሆናችን የሚመጣው ስድብና መደነቅ ለወንጌል በር ይከፍታል እንጂ ወንጌልን ያጭፈነፍናል ብየ አላስብም። በሕይወት ከመሰልናቸው ወንጌል ይደበዝዛል። ወንጌል ስለቱ ልዩትነቱ ነው። ይህንን ልዩትነት ማደብዘዝ፣ ማደነዝ ወንጌል እንዳይሰራ ማድረግ ነው።

*ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። (ገላ 5፡21)*

**የ**ዓለማዊነት ወላፈን ላንገበገበው ጥመኛ ሕያው ምንጭ የሆነውን ክርስቶስን እንድናቀርብለት ታዘናል እንጂ የዘፈንን በትሐ ጠጅ አጠጥተን እንድናሰክር አልተጠራንም ብየ አስባለሁ። ዘፋኝነትን ጳውሎስ እዚህ ዘፋኝነትን የጠቀሰው እንደ *ሥጋ ሥራ* ሆኖ ከሌሎች *የሥጋ ሥራ* ከተባሉት ጋር ዝርዝር ውስጥ ገብቶ ነው። ዝርዝሩ በአራት ነጥብ የተደመደመ ሳይሆን ሌሎችንም እነዚህን የመሰሉ ነገሮች የያዘ ነው። የተነጻጸረው ደግሞ ከመንፈስ ፍሬ ጋር ነው። ንጽጽሩ እጅግ ግልጽ ነው። የመንፈስ ፍሬ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚያፈራው ፍሬ ሲሆን፥ *የሥጋ ሥራ* ደግሞ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ወይም በመንፈስ የማይመላለሱና የሥጋን ምኞት የሚፈጽሙ ሰዎች (ገላ. 5፥16) *ሥራ* ናቸው። ዘፈንና እነዚህ *የሥጋ ሥራ* ተብለው የተዘረዘሩት ነገሮች የሥጋዊነት ጠባያት ወይም የሥጋዊ ሰው ባህርያት ናቸው።[30]

[30] ጋሽ ንጉሴ ቡልቻ በዘጸአት አፖስቶሊክ ቤተክርስቲያን "በዘፈን ጉዳይ" በተደረገ ፋናል ውይይት ሲያደርጉ ከተናገሩት የተወሰደ።

## 8. ለመንፈሳዊ ውጊያ ስለማይጠቅም

*“ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል።” (ያዕ 4፡7)*

**ዲ**ያብሎስን ለመዋጋት ሁለት ነገር ማድረግ ያስፈልጋል። ለእግዚአብሔር መገዛት እና ዲያብሎስን መቃወም ለውጊያ በጣም ወሳኝ ነው። ለእግዚአብሔር መገዛት ማለት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ነው። ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የዲያብሎስን ነገር ማስወገድ ያስፈልጋል። ሥጋን ይዞ ውሻን ማባረር እንደማይቻል ሁሉ እየዘፈኑ ከሰይጣን ጋር መዋጋት አይቻልም። የሰይጣንን ንብረት የሆነውን ዘፈን መጣል ግዴታ ነው። ስምንተኛው የማንዘፍንበት ምክንያት ለመንፈሳዊ ውጊያ ስለማይጠቅም አንዘፍንም! በቃ!

### ሦስት ምርጫ የለም

*በየ መንገዱ ወራጅ ምልቷል ተሳፋሪ፤*

*ከጠጣ በኋላ ወጭውን ሰባሪ፤*

*ትናንትናን አትርሳ አትሁን ውለታ ቢስ፤*

*ገባ ወጣ አትበል ጸንተህ ቁም በየሱስ፤*

*ያዝ ለቀቅ ሔድ መጣ ገባ ወጣ፤*

*ሕይወት ትርጉም ሲያጣ፤*

*ወይ ከየሱስ ወይ ከዓለም ምረጥ እንጂ፤*

*ሦስት መንገድ የለም።*[31]

*“በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ። ” (ዘዳ 30፡19)*

**ዘ**ዳግም ምዕራፍ ሥላሳ ከቁጥር አንድ ጀምሮ እስከ አስር ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ስለሚገኝ በረከት ይናገራል። ከቁጥር አስራ አንድ ጀምሮ በእስራኤላያዊያን ፊት ሁለት ምርጫ እንደቀረበላቸውን መጽሐፍ ይናገራል። በረከት እና መርገም። በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ስለናንተ

[31] የፓስተር ታምራት ኃይሌ መዝሙር።

ሕይወትን መርጭያለሁ አይልም። ሕይወትን ምረጡ ብሎ ምርጫቸውን እንዲጠቀሙ ይመክራቸዋል።

**ድ**ሮ ክርስትና ልዩ ውበት ነበረው ይባላል።[32] በዓለምና ክርስቲና በመሃል ቀይ መስመር ነበራቸው እነሱንና እኛን የሚለያይ ማለት ነው።[33] አንድ ወዳጄ የድሮ ክርስቲያኖች የቅድስና ሕይወት ደረጃ ሲናገር *"አንድ በጣም ሰካራም አጎት ነበረን ወደጌታ ና እሱ ይሻልሀል ስንለው እንዲህ ብሎ ነው የመለሰልን መጀመርያ እስኪወጣልኝ ልጠጣ ከዛ እመጣለው ነበር ያለኝ"* ብሎ ነግሮኛል። ምን ማለቱ እንደሆነ ግልፅ ነው። ማንም ወደ ክርስቶስ የሚመጣ ከስካሩ ጋር ሊመጣ ይችላል። ነገር ግን በስካሩ መቀጠል የለበትም። ክርስትና ከቀንበር ነጻ የሆነ ሕይወት ስላልሆነ የርኩሰት ቀንበር ሰብሮ የቅድስናና የጽድቅ ቀንበር መሸከም አለበት። ደስ ይበላችሁ ይህ አዲሱ ቀንበር ቀሊልና ልዝብ ነው።[34]

**መ**ዝሙርና ዘፈንን በአንድ ቀንበር ካልጠመድኩ፣ የጽድቅና የኃጢአት ቀንበር ከልተሸከምኩ፣ በሁለት መንፈሳዊ ስፍራ ካልሆንኩ፣ የክርስቶስም የቤልሆርም ካልሆንኩ የሚሉ "አማኞች" በድፍረት ሶስተኛ መንገዳቸው ላይ አብሮ የሚጓዙ ሰዎችን ከቤተክርስቲያን የሚመለምሉ እየታዩ ነው። ብርሃንና ጨለማ አለ። ግማሽ ብርሃን፣ ግማሽ ጨለማ ሊኖር አይችልም። አንዳንዴ ዘፍነን አንዳንዴ የምንዘምርበት ምንም ምክንያት የለም። እውነትና ሀሰት አለ። ግማሽ እውነት፣ ግማሽ ውሸት ሊኖር አይችልም። ዘማሪ(መጋቢ) ታምራት ኃይሌ *"ሦስት መንገድ የለም"* ብለው እንደዘመሩ ሶስት ምርጫ የለም። ከሁለቱ ሌላ ምርጫ የለም። ሶስት መንገድ እና ሶስት ምርጫ የለም። ምርጫው ግልጽ ነው። መዝሙር ወይም ዘፈን ነው።

**ዛ**ሬም ለክርስቲያኖች መዝሙርና ዘፈን የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሕልውና ጉዳይ ነው። ለእስራኤላዊያን በረከትና መርገም ምርጫ እንደሆነላቸው መዝሙርና ዘፈንም ለአማኞች ምርጫ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ፈቃድ ሰጥቷል። ፈቃዱ ፈቃዳችን እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን መዝሙር መምረጥ አለብን። ምንም እንኳን ተጽዕኖዎች ቢኖሩም ክርስቲያን ፈቃዱን ተጠቅሞ የፈለገውን የመምረጥ መብት አለው።

---

32 ለእውነት፣ ለጸሎት፣ ለፍትሕ፣ ለቅድስና እና ለቃሉ ያላቸው ቦታ ከፍ ያለ ነበረ(ይህ ማለት ግን አሁን ሙሉ በሙሉ ያን ጥራት አጥተናል ማለት አይደለም)። ሙስና ስለማይቀበሉ የደርግ መንግሥት ጴንጤዎችን ባይወዳቸውም በጉምሩኮችና ከፍተኛ የገንዘብ ነክ እንቅስቃሴ ያላቸው ቢሮዎች ውስጥ ይቀጥራቸው ነበር ይህ አንዱ ማሳያ ነበረ።

33 ልዩነት ስላለን ሄደን ወንጌል እንዳንናገር አይከለክለንም። ለወንጌል በር ይከፍታል እንጂ። በዓለም ውስጥ ብንኖርም እንደ ዓለም አንኖርም።

34 ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና። (ማቴ ፲፩፥30)

*"የሞቱ ዝንቦች የተቀመመውን የዘይት ሽቱ ያገሙታል፤ እንዲሁም ትንሽ ስንፍና ጥበብንና ክብርን ያጠፋል። የጠቢብ ልብ በስተ ቀኙ ነው፥ የሰነፍ ልብ ግን በስተ ግራው ነው።" (መክ. 10:1-2)*

**ጥ**ፋትም ድነትም ያልሆነ፣ አሉታዊም አዎንታዊም ያልሆነ፣ ጨለማም ብርሃንም ያልሆነ፣ ውሸትም እውነትም ያልሆነ፣ እኩይም ትክክልም ያልሆነ፣ ኩነኔም ጽድቅም ያልሆነ፣ ባርነትም ነጻነትም ያልሆነ፣ ኃጢአትም ቅድስናም ያልሆነ፣ ዓለማዊም መንፈሳዊም ያልሆነ፣ ከሰይጣኑም ከእግዚአብሔሩም ያልሆነ ሦስት መንገድ የለም።

**ገ**ለልተኛ ሰዎች የሚሄዱበት፣ ለዘብተኞዎች የሚቆሙበት፣ "Take it easy" የሚባልበት፣ አካብዴዎች የሌሉበት፣ ተቀላቅለው የሚነጉዱበት፣ ከዘፈኑም ከመዝሙሩም የሚባልበት፣ ሦስተኛ ምርጫ የለም። አራት ነጥብ። መምረጥ ግድ ነው።

## <u>ማጠቃለያ</u>

1. ሦስት ምርጫ የለም። ዘፈን ወይም መዝሙር ምረጥ?!
2. በጎ ነገር ብንናገር መጥፎ አይደለም። በጎ ነገር ለመናገር መዝፈን አለብን ወይ?
3. መጽሐፍ ቅዱስ ዘፈንን ሙሉ ለሙሉ ስለከለከለ፣ ሙሉ ለሙሉ ልንከፍተው አንችልም።
4. የማንዘፍንበት ስምንት ምክንያቶች፡-
   - ✓ ኃጢአት ስለሆነ
   - ✓ የእምነት አባቶች ስላልዘፈኑ
   - ✓ ከማንነታችን ጋር ስለማይሄድ
   - ✓ ስለማያንጽ
   - ✓ ከጥሪያችን ጋር ስለማይሄድ
   - ✓ ከአምልኮ ጋር ስለማይሄድ
   - ✓ ከወንጌል ምስክርነት ጋር ስለማይሄድ
   - ✓ ለመንፈሳዊ ውጊያ ስለማይጠቅመን

# ምዕራፍ አራት ቤተክርስቲያን ምን ታድርግ?

**ቤ**ተክርስቲያን ምዕመኖቿን ከተጋረጠባቸው የ"ዘፈናምነት"[35] አደጋ የመከላከል ውዴታዋ ብቻ ሳይሆን ግዴታዋም ጭምር መሆኑን መረዳት ይኖርባታል። ይህንን አደጋ መከላከል የምትችለው አማኞችን ደቀመዝሙር በማድረግ፣ ዘማሪዎች ከቃሉ እንዲዘምሩ በማድረግ፣ ለሙዚቀኞች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት እና እቅበተ እምነት አገልግሎት በማጠናከር ይመስለኛል።

## <u>አማኞችን ደቀመዝሙር በማድረግ</u>

**ደ**ቀመዝሙር ማለት የተማረ ማለት ሳይሆን የሚማር ተማሪ ወይም በመማር ሂደት ላይ ያለ ማለት ነው። ደቀ መዝሙር ቀን በቀን መምህሩን ለመምሰል በመምህሩ ትምህርትና አስተሳሰብ የሚቀረጽና የሚቃኝ ማለት ነው። እንደ መምህሩ የሚኖር፣ የሚያስተምር፣ የሚያስብ፣ የሚያገለግል የሚራመድ፣ የሚያወራ፣ የሚበላ፣ የሚሰራ... ወዘተ መላው እንቅስቃሴው እንደ መምህሩ የሆነ እርሱ እውነተኛ የመምህሩ ደቀ መዝሙር ነው። መምህሩ በውስጡ የሚታይ እርሱ እውነተኛ ደቀመዝሙር ነው።

**ቤ**ተክርስቲያን ምዕመናንን ደቀመዝሙር እንዲሆኑ ትኩረት አደርጋ መስራት አለባት። በየትኛውም የአገልግሎት ዘርፍ ከመሰማራት በፊት የሚቀድመው ደቀ መዝሙር መሆን ነው። ደቀ መዝሙር የሆኑ አማኞች ስለሌሉን ነው የአስተምህሮ ጥራት፣ የህይወት ጥራት እና የልምምድ ጥራት[36] የጎደለው። የአማኞች ደቀ መዝሙር ያለሆነ ህይወት በቤተክርስቲያንም አቅም ላይ አሉታዊ ተፅኖ እየፈጠረ ነው ያለው። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ከፊቷ ያለውን ዘፈናምነት አደጋ ለመትረፍ አማኞችን ደቀመዝሙርት ማድረግ አለባት።

## <u>ዘማሪዎች ከቃሉ እንዲዘምሩ በማድረግ</u>

**ክ**ርስቲያን ዘማሪያን ቀጠሮ ስለማክበር፣ ስለወንድማማችነት ፍቅር አስፈላጊነት፣ ስለቤተሰብ ፍቅር፣ ጠንክሮ ስለመሥራት ወዘተ (እንዲዘምሩ ማድረግ የእነዚህ ነገሮች ሁሉ መሠረት አምላካችን እግዚአብሔር እንደ ሆነ በሚያስገነዝብ መልኩ)። ችግሩ የአማራጭ መዝሙሮችን ማጣት፣ ወደ “መርጠን እንዝፈን” ወስዶን ከሆነ፣ መዝሙሮቹን እኛው ብናዘጋጃቸው ለተጋረጠብን “ዘፈናምነት” አደጋ መፍትሔ ሊሆን ይችላል ለማለት ነው።

[35] ቃሉን ከዘላለም መንግሥቱ ተጋርቸያሉ።
[36] “የአስተምህሮ ጥራት፣ የሕይወት ጥራት እና የልምምድ ጥራት” የሚሉ ቃላትን “የተሐድሶ ጥሪ”(መመርመር፣ መመለስ፣ መታደስ) ከሚለው ጥናታዊ ጽሑፍ የተጋራሁት ነው።

## ለሙዚቀኞች ተገቢውን ትኩረት መስጠት

**በ**ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለሙዚቀኞች ያለው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ ነው። ከዚህም የተነሳ ብዙ ሙዚቀኞች ዘፋኞች እና የዘፈን ስራ ላይ ተሰማርተዋል። እንደዚህ ዓይነት ክፍተቶች እንዳይፈጠሩ ቤተክርስቲያን ተገቢውን ትኩረት ማድረግ አለባት።

**ቤ**ተክርስቲያን በመዝሙር አገልግሎት እግዚአብሔርን የምያገለግሉ ሙዚቀኞች ሁለንተናዊ ሥልጠና የሚሰለጥኑበት ተቋም መገንባት አለባት ብየ አስባለሁ(ያሉትንም ማጠናከር ያጠቃልላል)። የሙዚቃ ትምህርት እየተማሩ በጎን የሥነ መለኮት ትምህርት የሚማሩበትን አማራጮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ሙዚቃ ብቻ ተምረው ሕይወታቸውን የሚመሩበት መንፈሳዊ እውቀት ካላገኘ ሰይጣን ጥቃቅን ምድራዊ ጉዳዮች በማቅረብና በማማለል ወደ ዘፈን እና ዓለም እንዳያስገባ ጥንቃቄ እና ተገቢ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል።

**ክ**ትትል ብቻ ሳይሆን ሰልጥነው የመጡ ሙዚቀኞች በአጥቢያ ቤተክርስቲያን አቅም በቂ ቀለብ ሊሰፈርላቸው ይገባል ብየ አስባለሁ።

## እቅበተ እምነት አገልግሎት ማጠናከር

**እ**ቅበተ እምነት አገልግሎት ማለት የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሙግቶችን በማዘጋጀት መሰረታዊ የክርስትና አስተምህሮን ከስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች መመከት ነው። መከላከል ላይ ትኩረት ያደረገ አገልግሎት ነው።

**ሐ**ዋሪያው ጴጥሮስም በመልዕክቱ *"ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ..."* (1ኛ ጴጥ 3፡15) ብሎ ሁሉም ክርስቲያን እምነቱ ላይ የሚቃጣ ኑፋቄን መመከት(መከላከል) እንደሚጠበቅበት ይናገራል።

**ክ**ርስቲያን መከላከል ብቻ ሳይሆን ሄዶ ማጥቃት አለበት። "ፖሌሚክስ"/Polemics የመጣውን የኑፋቄ ትምህርት መከላከል ሳይሆን ሄዶ ማጥቃት ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ የማይታወቅ አምላክ የሚያመልኩ የአቴና ሰዎችን ሄዶ የማይታወቀው አምላክ በማን እንደታወቀ እና ራሱን እንደገለጠ ተናገራቸው።[37] በቆሮንቶስ መልዕክቱም *"የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ <u>እናፈርሳለን</u> ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን*

[37] "የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ፡- ለማይታወቅ አምላክ የሚል ጽሕፈት ያለበትን መሠዊያ ደግሞ አግኝቼአለሁና፡- እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ። ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤ እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም።" (ሐዋ 17፡23-25)

*ሁሉ <u>እንማርካለን</u>”* (2ኛ ቆሮ 10፡5) ብሎ የሚከላከል ብቻ ሳይሆን ሄዶ የሚያፈርስ፣ የሚያጠቃና የሚማርክ “ፖሌሚክስ” አገልግሎት እንደሚያስፈግ እንመለከታለን።

**የ**ቤተክርስቲያን እቅበተ እምነት(በዘፈን ጉዳይ) መመንጨት ያለበት ከእምነቷ መሆን አለበት። እምነቷን ለመመከት ቁርጠኝነቱ ከሌላት፣ እምነቷ ከንቱ ነው። በትክክል እምነት ሲኖራት አይ፣ እምቢኝ የምትለው ነገር ይኖራታል። እዚህም፣ እዛም አትጣድም። ወይ እዚህ ነህ ካልሆነም እዛ ነህ ትላለች። ወይ ዘምር አልያም ዝፈን ትላለች። *“ዘፈን ኃጢአት አይደለም፣ መርጠን እንዝፈን”* የሚሉ ትምህርቶችን መከላከል ላይ ብቻ ሳይሆን ማጥቃት ላይም መስራት ይጠበቅባታል። የወንጌላዊያን ዓቅበተ እምነት/Apologetics ብዙ ጊዜ መከላከል ላይ ያተኩራል። ፖሌሚክስ ላይም ትኩረት መደረግ አለበት። እቅበተ እምነት ያለ ፖሌሚክስ አገልግሎት ስኬታማ ላይሆን ይችላል።

**ስ**ለዚህ ቤተክርስቲያን እንደ አንድ ኃላፊነት እንደሚሰማው መንፈሳዊና ምድራዊ ተቋም ቁጭ ብላ ልትመክርበትና ምትክ የሌለውን እምነቷንና አቋሟን በይፋ ልታቀርብና እርምጃ ልትወሰድ እንዲሁም የእቅበተ እምነትና ፖሌሚልስ አገልግሎት በአጥቢያ ደረጃ እንደ አንድ አገልግሎት ክፍል ወይም ዩኒት ማደራጀት አለባት ብየ አስባለሁ።

## ማጠቃለያ

1. ቤተክርስቲያን ምዕመኖቿን ከተጋረጠባቸው የ"ዘፈናምነት" አደጋ የመከላከል ግዴታ አለባት።
2. ከ"ዘፈናምነት" አደጋ መከላከል የምትችለው አማኞችን ደቀመዝሙር በማድረግ፣ እቅበተ እምነት አገልግሎት በማጠናከርና ለሙዚቀኞች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ነው።
3. በየትኛውም የአገልግሎት ዘርፍ ከመሰማራት በፊት የሚቀድመው ደቀ መዝሙር መሆን ነው።
4. እቅበተ እምነት አገልግሎት ማለት የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሙግቶችን በማዘጋጀት መሰረታዊ የክርስትና አስተምህሮን ከስሕተት ትምህርታትና ልምምዶች መመከት ነው።
5. “ፖለሚክስ” የመጣውን ማጥቃት ብቻ ሳይሆን ያለውን ሄዶ ማጥቃት ነው።
6. የወንጌላዊያ ዓቅበተ እምነት/Apologetics ብዙ ጊዜ መከላከል ላይ ያተኩራል። ፖለሚክስ/Polemics ላይም ትኩረት መደረግ አለበት።
7. የሙዚቃ ትምህርት እየተማሩ በጎን የሥነ መለኮት ትምህርት የሚማሩበትን አማራጮችን ቤተክርስቲያን ማዘጋጀት አለባት።

**(እኔ ባጎደልሁ መንፈስ ቅዱስ ይሙላበት። ኑሯችሁ ይባረክ!)**

# ዋቢ መጽሐፍት


- ቤት ያጣው ቤተኛ- በዮናስ ጎርፌ
- ቤት ያጣው ቤተኛ ሒሳዊ ግምገማ- ሐምሌ ፪ሺህ ፰ ዓመተ ምሕረት JULY 2016- ቁጥር ፴፫- በዘላለም መንግሥቱ
- “እየመረጥን እንዝፈን፣ እየመረጥን እንሞዝቅ!”- በዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ የተጻፈ ቅጽ
- እንዝፈን ወይስ እንዘምር- በዘላለም መንግሥቱ
- ዘፈን፣ ዘፋኝ፣ ዘፈናምነት- ዘላለም መንግሥቱ የተጻፈ ቅጽ
- ዮናስ ጄሐር አብደላ ገጽ
- www.youtube.com/Kiya_Show/Discussion_On_Zefen_Part_1
- www.youtube.com/Kiya_Show/Discussion_On_Zefen_Part_2